# ያገረሸበት ታሪክ

ያገረሸበት ሴራ አንፃር ጋህድ 1,2,3 መፃህፍቶች የተቀናጀ ዘመቻ ሲጋለጥ

1. ለኮኔረል ይትባረክ አማረ በስያትል የሚገኙ
2. ለሻኣብያ ታጋይ ነበር ሊንጎ
3. ለዓይጋ ዌብ ሳይት ( ሚድያ ባለቤት)
4. የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ሰራተኞች አቶ በትረስልጣንና አቶ ተወልደ ወልደገብርኤል።
5. ለድምፅ ወያኔ ትግራይ የህ.ወ.ሃት ሬድዩ ጣብያ
6. ለአቶ በርሄ ሓጎስ ታጋይ ህ.ወ.ሃ.ት ነበር ኋላም የደርግ ነጭ ለባሽ ሆነው ለትግራይ ህዝብ ያባሳብሱ አሁን በከናዳ የሚኖሩ
7. ከላይ ለተጠቀሱት ግለሰዎችና በስተጀርባ ሆነው በሉ እያሉ የሚገፍፋት የሻእብያ መሪዎች እና በኢትዮጵያ የሚገኙ ፓለቲካ ድርጅቶችና ባለስልጣናት
8. እንደነ አቶ ብስራት አማረ የቀድሞ የህወሓት የፀጥታ ሓላፊ (ፒአይ) ና የእሱር ቤቶች ሃላፊ የነበሩ በስተጀርባ የሚያደርጉት ግፊት ብስራት አማረ በ1984ዓ·ም በአ·አ ፀጥታና መረጋጋት ሆነው እየሰሩ የህዝብ የመንግስት መስራያ ቤቶች የኢሰፓ ባለስልጣናት በሚልዮን የሚቆጠር ዶላር ዘረፍክ ተብለው ለብዙ ወራት ታስረው ከቆዩ በኋላ ከባለስልጣኖች በነበራቸው ቅርበት ተፈተው ዶላሩን በተለያዩ ግዜና ምክንያት ወደ ዩ ኤስ ኤ አጉዘው ምንም ገቢ የሌላቸው በአገር ውስጥ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ኢንቨስት በማድረግ ይገኛሉ።አሜሪካ ሲኖሩ እንዴት እንደሚኖሩ በዳይስፖራ ያለው ህዝብ ያውቃችዋል።በኮሚኒቲዎችና በሶሊዳሪቲ ድርጅቶች ገብተው እየበጠበጡ መሆናቸውም ይታወቃል። የተሰጠ ግብረ መልስ

- የዚህ ፅሁፍ መነሻ አጀንዳ ኮኔረል ይትባረክ አማረ ስለ ጋህዱ መጽሀፍቶች ለሰጡት ትችት መነሻ ያደረገ ሆኖ በተጨማሪ የኮኔረል ይትባረክ ትችት እየተቀባበሉ የመፃህፍቶች ታሪካዊ ሃቅነት በመበላሸት ለተንቀሳቀሱ ግለሰቦች ለመግለፅና የሚያሰራጩት ያሉት ያገረሸበት ሴራ ለማጋለጥና ግብረ መልስ ለመስጠት ነው ቅድምያ ግን ታሪኮች ለመግለፅ እወዳለሁ ። ምክንያቱ አንባብያን ለነዚህ ኣካላት መንነታቸው ተረድታቹህ ትእዝብታችሁ እንድትሰነዝሩ በመፈለግ ነው ።

የቡድኖች ሂወት ታሪክ

1. ኮነሬል ይተባረክ አማረ ትውልድ ቦታ አክሱም አባታቸው መቶ አለቃ አማረ በሰባዎቹ  የቀይሽብር ተዋናኝ የነበሩ ከነበሩ ወደ ህወሓት የተቀላቀሉ በ1969 ዓ.ም ማዝያ ወር በዛን ግዜ በ92 ሻንበል ተመድበው እያሉ በህወሓት ድርጅት አውራጃውነት የሚሉት ቀውስ ተፈጥሮ በነበረበት ኮኔረሉ በዛ ወቅት ለነዚ ዲሞክራሲ ጥያቄ ያነሱ ቡድኖች ታጋዮች በመጋለጥና እነዲታሰሩ እንዲቀጡ የበቁ ሰዎች በመወንጀልና በመጋለጥ ትልቅ ሚና የነበራቸው ። ኮኔረሉ በሃይል 92 ተጋዮች ተወዳጅ ስላልነበሩ በ1970 ዓ.ም ሕዳር ወር ወታደራዊ አሰልጣኝ ሊሆኑ 02 (ማሰልጠኛ ጣብያ) ተላኩ ። የአሰልጣኝ ስልጠና ሰጥተናቸው የአንድ ጋንታ (40) ስልጣኞች መሪ ሆኑ ። ቀስ በቀስ ከብዙ አመታት በሓላ ረዳት አሰልጣኝ (እንስትራክተር ) ሆኑ ኋላም በማሰልጠኛ ጣብያ ለስለጣኞች ከሻንበል አዛዥነት እስከ ብርጌድ መሪ ሆኖ በ1982 ዓ.ም የማሰልጠኛ አመራር ኮሚቴ ሆነው ነበር።

- በ1982 ግማሽ አካባቢ ወደ ተዋጊ ሰራዊት ተመድበው የብርጌድ ፓለቲካዊ ሃላፊ ሆነው ነበር ወደ 1983 ዓ.ም መጨረሻ ክፍለጦር ፓለቲካዊ ሃላፊ ሆነው ነበር ከደርግ ውድቀት በኋላ ብዙ ሚና አልነበራቸውም ። በሰራዊቱ እያሉ የዘመኑ በሽታ አጋጥማቸው ለህክምና ወደ ጀርመን ተልከው በዛው ከባለስልጣኖች ካላቸው ቅርበት የተነሳ በኢንባሲው ሚሊተሪ አታሽ ተመድበው እየሰሩ እያሉ በዛው የነበረ ገንዘብ አፍሰው ይዘው ወደ U S A ስያትል ተሻገሩ ጥገኝነትም ጠየቁ ተሳካላቸው በአሜሪካ ስራ የሌላቸው በአሜሪካ ስራ ለሌላቸው በመንግስት የሚሰጥ ገንዘብ እየተከፈላቸው እየኖሩ ለወደፊት ጡረታ አግኝተው ወደ ኢትዮጵያ ምህረት ለመግባት እየተዘጋጁ ናቸው ፤፤ ከተሳካላቸው።
- ኮኔረል የትባረክ አማረ ቅፅል ስማቸው ተክለ ጎረሳ ይባላል ይህ ስም የተሰጣቸው ዝምብሎ አይደለም።በሽሬ አውራጃ በሰለክለካ በእንዳስላሴ የሚኖሩ ኣንድ በአእምሮ ያዘገመ ተክለ ጎረሳ የሚባል በልቶ ጠጥቶ የማይጠገብ ምግብ የማይበቃው ስራ ያልከው የሚሰራ ተናገር ያልከው የሚናገር ቅርፅ ሰውነት ከኮኔረል ተመሳሳይ የነበረ ከተኛ ተነሳ ስትለው በቀላሉ የማይነሳ ነበር የሚናገረው የማያመዛዝንና የሚመሰለው የሚናገር የአእምሮ ችግር የነበረው ነው ፤፤ ኮኔረል ይትባረክ (ተክለ ጎረሳ) ከታገለበት ጊዜ ጀምረው ተመሳሳይ የተክለ ጎረሳ ባህሪ ስለነበራቸው በማሰልጠኛ ጣብያው ስም ወጣላቸው ።
- ኮኔረል ይትባረክ (ተክለ ጎረሳ በትግሉ ወቅት ይሁን ትግሉ በሓላ በነበሩ የሰብሰባ መድረኮች ፣ጉብአዎች ኮንፈረሶች ፣ስሚናሮች ካድረ ትምህርት ቤቶች በተለይ ደግሞ በየአመቱ የሚከፈቱ ድርጅት ለማጥራት በሚል ሰበብ የሚከፈቱ መድረኮች ብዙ ታጋዮች የሚታሰቡትን (የሚቀጡበት)ኮኔረል ተክለ ጎረሳ ዋና ተዋናኝ ነበሩ ኮኔረሉ የማመዛዘን

ችሎታቸው እጅግ እጅግ ዝቅተኛ ነው ኮኔረሉ ለመሪዎች ያስደስታል ያሸማል ያሉት ሁሉ ያደርጉ ነበር ።

2. በትረ ስልጣን የአሜሪካ የድምፅ ሬድዮ የትግርኛ ቃንቃ ቡድን መሪ ይህ ሰውዮ አገሩ የት እንደሆነ አላውቀው ግን ደግሞ በኢትዮጵያ የሚገኙ ፓለቲካዊ ፓርቲዎች አባል መሆኑና የነሱ መልእክተኞች ሆኖ ድምፅ ሬድዮ አሜሪካ ለግለሰዎችና ፓለቲካ ፓርቲዎች መምቻ የሚጠቀምበትና ኮኔረል ይትባረክ (ተክለ ጎረስ) ጎን ቆሞ በያገረሸበት ሴራ ዋና ተዋናይ ሆኖ ቆማል ። በትረስልጣን ድምፅ ሬድዮ አሜሬካ እንደ ግሉ ተቃም እየ ተጠቀመበት እንደመጣ ትግርኛ ቃንቃ ተናጋሪዎች በጥላቻ እንደሚያዩትና በትግራይ ምንም ሰሚ (አዴንስ) አጡታል ይህ ጉድ የድምፅ ሬድዮ አሜሪካ ዋና ፅሕፈት ቤት አውቆ ማገቻ ማድረግ አለበት ከለበለዝያ ድምፅ ሬድዮ አመሪካ በትግራይ ህዝብ ተቀባይነት የለውም ።
3. ተወልደ ወልደገብርኤል እንደበትረ ስልጣን የሻአብያ ህግደፍ አባል ነው እንደበትረ ስልጣን የሻእብያ አፈቀላጢ ሆኖ ጋህዲ መፃህፍቶች ለሻአብያ ሴራው ስለአጋለጡ ኮነሬል ይትባረክ በትረ ስልጣን ጎን ሆኖ እየታገላቸው ነው ሃቂ ግን ያገረሸበት ያለው ሴራ መባባስ አልፎ የሚሚፈይደው ነገር የለም
4. ድምፅ ወያነ ትግራይ የሓላ ታሪክ በተለይ በዘመነ ደርግ ፋሽሽታዊ ስርዓት ለማስወገድ በተደረገው ትግል ህዝብ ተቅቶ ፣ተደራጅቶ ታጥቆ ወደ ትግል እንዲዘምት በማድረግ በፍክለ ጦር ክብር በግብረ ሃይል የማይለካ የፕሮፓጋንዳ ውግያ ትልቅ ውጤት ነበረው ። በአሁኑ ወቅት ግን ደረጃው ወርዶ የአንድ ፓርት ህወሃት ኢህወደግ ብቻ እያገለገለ እንደዚሁ እንደነ ኮነሬል ይትባረክ አማረ ርካሽ ትረካ እንደትቦ በመስተላለፍ ፀረ ጋህድ መፅሓፍቶች ዘመቻ በማካሄድ ስንብቷል ።

- ድምፅ ወያነ ሬድዮ ጣብያ ጋህድ 1,2,3 በመቀሌ በሚላኖ፣ ሃፀይ ዮሃንስ ሆቴሎች ሲመረቁ ጥሪ ተደርጎለት አልተገኙም ፍቃደኛ ስላልሆነ።
- በአንፃር ይዘታቸው ምን ይሆኑ ምን ለእንደፅናት በአቶ ስዩም መስፍን ታሪክ የተተረከ በብዙ ውሸት የታጀበ ፣እንደ የትግራይ ህዝብና የትምክህተኞች ሴራ የሚል የኢትዮጵያ አንድነት የሚያናጋ በመምህር ገ/ኪዳን ደስታ የተፃፈ ፣እንደ አይንተሓማመ (አንተማማ) የሚል ህዝቦችን የሚነጣጥል በአታክልቲ ሃጎስ የተፃፈ እንደ እነ ጊላህቲ ስጊና መለሰና የህ.ወ.ሃ.ት ጉዞ የሚሉ ሌሎችን መፃህፍቶች ቀናት ፣ሳምንታት ፣ሳይሆን ለወራት ያህል በመደስኮር ሲያስደነቁረን ኖሮ ለጋህድ መፃህፍት ፊት ለፊት እንደይገጥም ሃቂን የትግራይ ህዝብና የህወሓት ታጋይ የኤርትራ ህዝብና የሻአብያ ታጋይ የሚያውቁት ታሪክ በመሆኑ ዝምብሎ ቆይቶ አሁን ኮኔረል ይትባረክ ( ተክለ ጎረስ) የምህረት ካርድ ለማግኘት የሚደሰኩሩት በማንጠለጠል ያን የነበረው ክብር እየቀንስና የህዝብ ትግራይ የህወሓት ታሪክ እያድበሰበሰ ይገኛል ።

- ድምፅ ወያነ ከደርግ ውድቀት በሓላ ለትግርኛ ተናጋሪዎች ህዝቦች በቅን ማገልገሉ ቀርቶ ለገነኑ መሪዎች ስመጥሩነት ያደረጉት ያላደረጉት ሁሉ ማሽሞንሞን ውጭ በክልላችን ያሉት አፈናዎች ኢ-ዲሞክራሲ የሆኑ ተግባሮች ሙስና ፍትህ መጋለጥ በሚመለከት መናገር መንግስትን እንደመገልበጥ ቆጥሮች አንድን ቃል ተናግሮ አያውቅም ፡፡
- ሌላ ቀርቶ በክልላችን በሽሬ አውራጃ የሚገኘው ሰው ጨራሽ በሽታ በሚመለከት አንድም ቃል ተንፈሶ አያውቅም
- በህብረተሰቡ የሚታዩ እንደ ስራ አጥነት ፣መልካም አስተዳዳሪ እጦት ፣ስለ ፀጥታና ፍትህ ፣ ስለ ድርቅና ተላላፊ በሽታዎች ተንፍሶ አያውቅም ፡፡
- ምርጫ በሚመለከት 24 ሰአታት ለገዥው ፓረት በመቁም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስም ማጥፋትና በህወሓት ሊመቱ የሚፈለጉ ግለሰዎችና ቡድኖች መቺ ሃይል ሆኖ ተገኝተታል
5. በርሀ ሃጎስ የሓላ ታሪኩ ተማሪ ሁኖ በረሀ እየወጣ ብረት ታጥቆ ህዝብ በመስፈራራት ገንዘብና ፍዮሎች ይነጥቅ ነበር በ1968 ዓ/ም በህወሓት ተይዞ ከገበሬ ነጥቆ ያረዳት ፍየል ቆዳ ለብሶ በህዝብ ሬት የቀረበበት ጊዜ ነበር ፡፡ ሓላ እታገላለሁ ብሎ ህወሓት ተሰልፎ እስከ ምክትል ሃይለ መሪ ስልጣን ደርሶ ሓላ በጦርነት ስለሸሸ ህወሓት ከድቶ ወደ ድርግ ገብቶ የትግራይ ነጭ ለባሽ መሪ ሆኖ ብዙ የከተማና የገጠር ህዝቦች ያሳቃዮና ያበሳበሰ ሰው ነው ፡፡ አሁን ለገዥ ፓርቲ ህወሓት ምህረት ለማግኘት ይመስል ለጋህዲ መፃህፍቶች ሃቀኝነትን ለመባለሸት ከኮነሬል ተክሌ ጎረሳ እየተንቀሳቀሰ  ይገኛል በርሄ ሃጎስ ኢትዮራስ አሉላ አባነጋ በሚለ ፓልቶክ በመጠቀም አንፃር ጋህዶች እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡
6. የአይጋ ወቭሳይት ባለቤት ይህ ሰውዮ ቀደም ሲል በደርግ ስርዓት ወቅት ካድረና የድህነት ሰው በመሆን ህዝብ ሲያሳቃይ የነበረ ነው አሁንም የገዥ ፓርቲ መሳርያ በመሆን እየሰራ ይገኛል ፡፡ አሁንም የህዝብና የፓለቲካ ድርጅቶች ሃቀኛ ታሪክ ለፃፍ ሰዎችና መፃህፍቶቻቸው ስምን ለመባላሸት የነኮኔረል ይትባረክ ቁሸሽ ፅህፎችን በማሳተጋባት በያገረሸበት ሴራ ተስማርቶ ይገኛል
- እንግዲህ ላይ የዘረዘርኩዋቹው ፀረ ጋህድ መፃህፍት የሚንቀሳቀሱ ቡድኖችና ብዙሃን መገናኛ ነን ባዮች አጭር ታሪክ ከስቀመጥኩ ዘንድ ወደ ዋና ፅሁፍ የሆነው የኮነሬል ይትባረክ አማረ ፅሁፍ በአይጋዌቭ ሳይት የፃፍት ልግባ ፡፡
- ኮኔረል ይትባረክ በትግርኛ ብድህረይ ዳንዴር አይትውቀላ (እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቆል) በሚል አርእስት ያለው ፅሁፍ 19 ገፅ አንፃር ጋህዲ መፅሃፍ በዓይጋ ዌቭሳይት ድህረ ገፅ እንደስቀመጠው ከፍ ብሎ ተጠቅሳል ፡፡

- ይህ ፅሁፍ በትግርኛ የተፃፈ ነው እኔም ይህ ፅሁፍ በትግርኛ መልሰ ከመስጠት በአማርኛ መልስ ልሰጠው ስለፈለግኩ እንሆ መልሱን ገፅ በገፅ መስመር በመስመር መልስ እሰጠውአለሁ ።
- በአማርኛ መልስ ልሰጠው የፈለኩት 1ኛ ጋህዲ አንድ በህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ ህወሓት ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ ሕግ.ሓ.ኢ. የነበረ ግንኙነት ከጥዋቱ ጀምሮ በጌታና በሎሌ የተመሰረተ ግንኙነት ነው የሚለው ስለሁለት ድርጅቶች የተቀናበረ ሴራ የሚተነትን ትረካ
- 2ኛ ጋህዲ ሁለት ህ.ወሓት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 1977 ዓ/ም የሰራዊት ህወሓት አፈጣጠሩና ግንባታው፣እድገቱ በሚሉ ርእሰ ገፅ 466
- 3ኛ ጋህዲ ሦስት ህወሓት አሁንም ህንፀት ሰራዊት ህወሓት አፈጣጠሩ ግንባታና እድገት በሚል ከ1977 ዓ/ም አጋማሽ እስከ 1994 ዓ/ም በሚተረኩት መፅሃፍቶች በትግርኛ መልስ መስጠት ትግርኛ ተናጋሪዎች ብቻ ለምን ያውቁታል ታሪኩ ኢትዮጵያዊ እያለ ሁሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ባለጉዳይ እያለ ለምን አያውቁውም እስከአከአሁን የነበረው ደቡቁኝ ደቡቁኝ በሚለው ሴራ ለምን አይገረሽም የትግራይ ህዝብ ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ አይደለምን ወይ ፣የአማራ ፣የአፋር፣ ሱማል፣ ኦሮሞ ፣ ደቡብ ፣ጋንቤላ ህዝቦች የሰሩት ታሪክ የኢትዮጵያ ታሪክ አይደለም ወይ በሚል እምነት ለምን በ4 ሚልዮን የትግራይ ህዝብ ታጥሮ ይቀራል በሚል እምነት ስለሆነ እንሆ ለመላው ባለጉዳይ የሆንከው ኢትዮጵያዊ አስተላልፈውአለሁሉ ።
- <u>ወደ ግብረ መልስ ለመግባት</u>
- ኮኔረል ይትባረክ በፅሀፋቸው በሁለቱ ድርጅቶች የነበረ ግንኙነት በጌታና በሎሌ የተመሰረተ ግንኝነት ነበር ለሚለው በንዴት ኢትዮጵያዊ ጭዋነትና ግብር ገብነት በጎደለው በንግግራቸው ብዙ ብለዋል ። በተለይ ቀደም ብለው በበርሂ ሃጎስ ፓልቶክ ቆይቶውም በሬድዮ ድምፅ አሜሪካ በአጋራቸው በትረሰልጣን በጋህዲ መፅሀፍቶች ተዘጋጅቶ የተሰጠው ጥያቄ ሲመልሱ፡ ሓላም በዓይጋ ዊቨሳይት በበተኑት ፅሁፋቸው ብዙ ያልታረመ በውሸት የታጀበ ያገረሸበት ሴራ ለብዙ ሰው ጀሮ አደንቁራል ። አሰላችቷልም በዚ መሰረት በማድረግ አንድ በአንድ መልስ እስጥበታለሁ ።
- ኮኔረል ይትባረክ (ተክሌ ጎረሳ) በገፅ አንድ ፅህፎቸው ይላሉ ፣በመጀመርያ ለገልፀው የምፈልገው ታሪክ የሰራ ትውልድ በሂወት እያለ አስገደ ጋህዲ የሚል አርእስት ያለው በፈጠራ ትያትር እየሰራ ነው ይላል ለአስገደ የፈጠራ ታሪክም መልሰ ሊሰጥ የሚችል ስለታጣ መልስ ለመሰጠት ተገደድኩ ይላል ።
- ኮኔረል የፈጠራ ታሪክ ሲሉን ምን ማለታቸው ነው ጋህድ አንድ መፅሃፍ የፈጠራ ታሪክ ነው ካሉ ከምን ተነስተው ነው ? በዚህ መፅሃፍ የተቀመጠው ታሪክ ሃቅ መሆኑና አለመሆኑ ይቅርና የትግራይ ህዝብና የህወሓት ሰራዊት የኤርትራ ህዝብና ቅንነት ያላቸው የሻእብያ ተጋዮች ፣ሌሎች

በአካባቢያችን የነበሩ ፓለቲካዊ ድርጅቶች የሚመስክሩት ነው ። ስለሆነ ወደዱም ጠሉም በሁሎቱ ድርጅቶች የነበረ ድብቅ ሴራ እንዳይገለጥ ለመሸፈንንና ላይ እንደገለጥኩት የመዘበሩት የህዝብ ዶላር በለተው ስለጨረሱት ወደ አጋራቸው ምህረት ገብተው ጥሮታ አበል ይዘው ለመኖር ስለፈለጉ ነው ።

- ቀጥሎ በገፅ አንድ አዲስ መስመር ሁለት ፣አስገደ ከሀሰት ድርሰት በመደጋገም በ.ህ.ወ.ሃት ህ.ግ.ሓ.ኢ. የነበረ ግንኙነት በጌታና በሎሌ (አብ ጎይታን ጊላን) ነው የነበረ ይላል ። በመቀጠል የኢትዮጵያ ህዝብና የትግራይ ህዝብ ራሳቸው የኤርትራ ህዝብና ሻእብያ የሚመሰክሩት የትግራይ ህዝብና ከሱ የተወለደ ህወሃት የኢትዮጵያ ህዝብ ከአኝከርነት (ሎሌነት) ነፃ ለማስወጣት በኢትዮጵያ ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ጀግንነት የሰራ ለሸአብያም ከመቃብር ያወጣበት ጊዜ ነበር በአጠቃላይ ትምክህት አይምሰል እንጂ የትግራይ ህዝብ ወይም ህ.ወ.ሃት ከሚሉ ቃላት ሌላ(አሽከር ) ከሚሉ ቃላት አይስማማም ። የዛሬ ብቻ ሳይሆን የጥንት ታሪካችን የሚያረጋግጠውም የትግራይ ህዝብ አንድ ደቂቅ ሎሌ ሆኖ አያውቁም ይላሉ ።
- ኮኔሬል ( ጎረሳ) የትግራይ ህዝብ በአጠቃላይ ህዝብ ጀግና የማይምበረከክ መሆኑ ሎሌ ሆኖ እንደማያውቅ እኔም እስማማለሁ እኔ በመፅሃፍ ( ሰነዱ) ያስቀመጥኩት የትግራይ ህዝብ የህወሓት ታጋይ ጀግና ነው ለፍሽሽት ደርግ ያሸነፈ ነው ደርግ ለመደምሰስ ብቻ ሳይሆን የሻአብያ ሎሌ በሆነው የህወሓት አመራርና ታማኝ ካድሬዎች ተገዶ በኤርትራ በረሃዎች ለሻአብያ ለማደን ከባድ መስዋእትነት ከፍለዋል ። በሁሉም መፅሓፎቶቼ ህዝብና ታጋይ ህወሓት ሎሌ ነበር አላልኩም ሁሉም አንባቢዎች ይመሰክራሉ የህወሓት አመራር ግን ህወሓት ከተፈጠረችበት ጊዜ 1967 ዓ/ም ጀምሮ እስከ መጨረሻ የሻአብያ ታማኝ ሎሌ እንደነበር ብዙ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉ በጋህድ አንድም በዝርዝርና በጥልቀት በስፋት ተገልፀዋል።በጋህድ ሁለትና ሰዎስትም ጠለቅ ባለ መንገድ በማስረጃ የተረጋገጠ ተገልፆል ።የተከበራችሁ አንባብያን የህወሓት አመራር ለ17 አመት ሎሌ ሆኖ የቆየበት ጊዜ እንተወውና በ2000 ዓ/ም አቶ ስብሃት ነጋ ስለ ኢትዮጵያ ባህር በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦላቸው የባህር ጉዳይ መነሳት የለበትም ኤርትራ ነፃ ሃገር ስለሆነች ባህሩም የኤርትራ ነው የኤርትራም ነፃነት ለማስመጣት ብዙ መስዋእቲ የከፈለንበት ነው ።አሁንም ቢሆን የኤርትራ ነፃነት የሚነጥቅ ሃይል ከመጣ ከምንጠላው ሻእብያ ጎን ተሰለፈን እንዋጋለን ብለዋል ።ታድያ ኮኔረል ጎረሳ የአቶ ስብሃት ነጋ አነጋገር ሎሌነት አያስብለም ?እስቲ ፍርዱ አቶ ስብሃት አሁንስ የማን ልጅ ወደ እሳት ሊማግዱ ናቸው ።
- <u>ኮኔረል በ ገፅ አንድ </u>አዲስ መስመር 3 መስመር 7

- በአስገደ ቁጥር አንድ መፅሃፍ ተጀምራ እስከምትጨረስ ህ.ወ.ሓ.ት የሻእብያ አሽከር(ሎሌ) አገልጋይ እንደነበር ይገልፃል ከዚያ አልፎ አስገደ ታጋይና የትግራይ ህዝብ ኣመራሩ የሻአብያ ትእዛዝ አስፈፃሚ እንደ ነበረ ይገልፃል ያሳዝናለም ይላል ጎረሳ ፡፡
- ሁላችሁም አንባቢዎች ሃቁን መስክሩ ኮኔረል ሲናገሩ ሲበሉ ሲጠጡ ለነገ እንደማይሉ ሁሉ ቶፊጥሮአቸው ሆኖ ነው ይመስለኛል በመፅሓፍ የሌለ ፅፈዋል ፡፡በመፅሃፍ የትግራይ ህዝብና የህ.ወ.ሃት ጀግንነት የችግር ቻይነት ልጆች ንብረቱ ራሱ ለትግል በመሰጠት ለደርግና ለሌሎች ሃይሎች ያሸነፈ ጀግና ወ.ዘተ በሚሉ በመፅሃፍ ተሰንዷል ፡፡ በመፅሃፍ ለይቶ በጠራ መንገድ የህ.ወሓት ማእከላይ ኮሜቴና ጥቂት ካድሬዎች የሻአብያ ሎሌዎችና ታዛዦች ነበሩ ብያለሁ አሁን እምነቴ ነው ፡፡
- <u>ለዚህ እንደ ማስረጃ</u>

1. አቶ ገሰሰው አዩለ ንፁህ ኢትዮጵያዊና ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት ሉኣላዊነት ብልፅግና የቆሙ ስለነበረ በመጀመርያ ደደቢት እንደወጣን ስለኤርትራ ነፃነት ሲነሳ ተው የኤርትራ መገንጠል ጉዳይ ታሪክን አጥንተን ቀስ ብለን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸውን እንመካከርበት የሚል ጥያቄ ያነሱ ስለነበር ይህ ጉዳይ ሻአብያ ታሪኩ ያውቁ ስለነበር ፡፡

1.1 አቶ ገሰሰው አዩለ የህ.ወ.ሓት ሊቀመንበር በነበሩት ስብሃት ጃማይካ አስከትለው ከሻአብያ ግንኙነት ለማጠናከር ሳህል ሲሄዱ ሻአብያ ለአቶ ገሰሰ በማግለል የአቶ ገሰሰ አጃቢ ሆኖ ከሄደው ስብሃት ነጋ ተገናኝተው ለአቶ ስብሃት የቤት ስራ ሰጥተው አቶ ገሰሰ ምንም ግንኙነት ሳያደርጉ ተመለሰው መጡ ፡፡

1.2 በጥቅምትና ሂዳር ወር 1968 ዓ.ም ታማኝ ለሁኑት የህወሓት አመራር በሻአብያ አማራር የተሰጠ የቤት ስራ ገሰሰው አዩለ የኤርትራ ነፃነት ስለማይቀበል ፀረ የኤርትራ ህዝብ ስለሆነ ከህ.ወ.ሓት አመራር እና ከድርጅት አመራር አባረሩት ግንኙታቸው መልካም ሊሆን ከተፈለገ የሚል ትእዛዝ ተሰጣቸው ይህ ምስጢር ደጉተር ግደይ ዘርአፅዮን ደጉተር አረጋዊ በርሄ አቶ ስብሓት ነጋ አቶ አባይ ፀሃዮ አቶ ስዮም መስፍን በሂወት ያሉ ያውቁታል ፡፡ በመሆኑም አቶ ገሰሰ ህወ.ሓት አመራር ቡድን በመፍጠር እንዲገለል ተደርጋል ፡፡

1.3 ህ.ወ.ሃት በእንጭጩ፣ የካቲት 11/6/67 ዓ/ም ደደቢት የወረደ በሚያዝያ መጨረሻ ሃይለ በርሀ በአድዋ ዓድአቡን ገ/ማርያም ክሕሸን ብሃውዜን ወዲ ህወሓት ከተቀላቀሉ በኋላ ስለ ኤርትራ ነፃነት እንዴት ታሪካዊ አመጣጡ የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ጥያቄ አንስተው በዛው የነበረ የህወሓት ጊዜያዊ አመራርና የነሱ ተከታዮች ለምን ይህ ጥያቄ አነሳቹህ ተብለው ኣላአስፈላጊ ዛቻና ማስፈራራት ስለደረሰባቸው

ሰግተው ተሰወሩ ሃይለ በርሀ በአሜሪካ አገር ይገኛል ለህሊናው ይመስክር

1.4 የህወሓት መሪዎች መጀመርያ ከሻአብያ ሲገናኙ የሻአብያ መሪዎች ወደ ትግሉ የምታሳትፉት ሙሁር ሃይል ከሆነ መጥፎ ነው ቀውስ ፈጣሪና አንጃን እየፈጠረ ይበጠብጣቸዋል ።ስለዚህ ድጋፍ ልንሰጣቸሁ ከፈለጋችሁ ገበሬ አሰልፉ የድርጅት  የጀርባ ኣጥንት ሊሆን የሚችል ገበሬ ነው ከኛ ተማሩ አለበለዝያ ድርጅታችሁ ሙሁር የበዛበት ከሆነ ድጋፋችን አንሰጥም ሲላቸው እሽ ብለው ተቀብለው ለተግባራዉነት ተንቀሳቅሰዋል ። ታድያ ይህ ጉዳይ ታዛዥነት አይደለም  ? ሎሌ አያስብልም ?

1.5 አቶ ኢሳእያስ ለነዛ ሊሰለጥኑ ተብለው ወደ ሳሕል በአቶ ስዩም መስፍን ተመርተው ተጉዘው ያቺ የማትረባ ወታደራዊ ስልጠና 17 አሮጌ ብረት ሰጥተው ሲሸኛቸው ድርጅታችሁ በአንድ መስፍን ገሰሰ አየለ ነው የሚመራ የሚል ወሬ ስላለ ጀማይካ (የማነ ኪዳነ) የሚባል ሊያጠናቸው አጥንቶ ከመጣ ካረጋገጥን በኋላ ድጋፍ እናደርግላቿለን ብሎ ግልፅ ሰላይ እንደሚልክ ሲነግራቸው የተባለውን ትእዛዝ የመቀበል ልምድ የተጠናወተው የህወሓት አመራር በሰላዩ ጀማይካ ታጅቦ ደደቢት ደረሰ ። ስለዚህ ጉዳዩ የማነ ኪዳነ (ጀማይካ ) በጥሕሎ መፅሄት በትግርኛ የሚዘጋጅ

❖ በ2000 ዓ/ም ራሱ በመሰከረበት ኢሳእያስ አፈወርቅ ለሰለላ እንደላከው አምናል ። ታድያ ኮኖሬል ይትባረክ ይህ ሎሌነት አይደለም የህወሓት አመራር በራሱ መተማመን የነበረበት ነው የሚሉን ይህ ነው አንባቢያን ትእዝብታቹህ አሳርፉበት

2. ኮነሬል ይትባረክ (ጎረሳ) በገፅ ሁለት ፅህፋቸው በጥያቄ መልክ እንዳሰቀመጡት ይላሉ ።

- ህወሓት ወደ ሻአብያ ለወታደራዊ ስልጠና ሰልጣኞች መላኩ ለህወሓት የሚጎዳ ለሻአብያ የሚጠቅም ነው የሚለን ለጃብሃ ኤርትራ ተሻግሮ ማጥቃቱ ወደ ኤርትራ ዘምቶ ለደርግ መምታቱ በዘመቻ ቀይ ኮከብ ሻአብያን ለመርዳት ወደ ሳህል ሰራዊት ማስገባቱና ለደርግ መደምሰሱ ህወሓት ለመጥቀም ወይስ ሸአብያ ለመዳን በዘመቻ ቀይ ኮከብ ወቅትና ስላሕታ ወራር ጊዜ ሃያ ሰባት (27 ሽህ) ሰራዊት ሞታል ቆሱላል ይላል ለመሆኑ ህወሓት በዛን ግዜ ያን ያህል ሰራዊት ነበረው ወይ? አሰገደ ለዚህ ለማወቅ የሚያስችል ስልጣንና ቦታ ነበረው ወይ አስገደ በዛ ጊዜ የት ነበረ በትግራይ በሱዳን በኤርትራ ይላሉ ኮነሬል (ተክለ ጎረሳ ,ይትባረክ)
- ላይ ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች አንድ በአንድ ይድረስ ለአንባብያን

2.1 ሀ.ወ.ሃ.ት ወደ ሻአብያ ሰልጣኞች መሰደድ ለጀማሪ ድርጅት ይጠቅመዋል እኔ እምለው ሻአብያ የሰጠው ስልጠናና ድጋፍ ለህወሃት ጥገኛ የሚያደርግና ከጥዋት ጀምሮ የሻአብያ አመራር ለህወሃት

አመራር ባዘዝናቹህ ሂዱ ካለሆነ አናግዝም ሲላቹ የህወሓት መሪዎች በራሳቸው እምነት አልሄዱም ተንበርክከዋል ሎሌነታቸው አረጋግጠዋል።

2.2 ሀ.ወ.ሃ.ት ከጀብሃ ጋር የነበረው ግንኙነት መጀመርያ ጀምሮ ጥሩ እንዳልነበረ እኔም አውቃለሁ ። በጅብሃና በህወሓት የነበረ ግጭት ሻእብያ የሚፈጥረውና የህወሓት አመራር ከጅብሃ ሻእብያ ነው ተራማጅ ጅብሃ አድሃሪ ነው እያለ ። ሻእብያ ምንም ተራማጅነትን ያልነበረው ጅብሃም እኔ ነበር ድርጅት የድርጅቶች አባት ፣እናት እያለ በትምክህት ይደናፋ ስለነበር በህወሃትና ጅብሃ መቃቃር እንደነበረ አውቃለሁ ሻእብያ ሲፈጠር ለነበረው መቃቃር ለህወሃት መሪዎች በመገፋፋት ያባብሰው ነበር ። ዋና ጥያቄ ለምን ጅብሃ ተመታ ነው ።

- ህወሃት ሻእብያ ከ1967 ክረምት እስከ 1968 ሰኔ 12/10/68 ዓ/ም ግኑኝነታቸው ሞቅና ቀዝቀዝ እያለ ተጉዞ ከራዘና ነበልባል ዘመቻ በኋላ ፍፁም ተጣልተው ሻእብያ ከሀ.ወ.ሃት የነበረው ግኑኝነት አቃርጦ በኢ.ህአፓ ጋር ግንኙነቱ በማሞቅ ተንቀሳቀሰ።
- ይባስ ብሎ ህወሃት ከኢ.ድዩ የተጋጋለ ጦርነት በነበረበት ሻእብያ ኢ.ህአፓ ጅብሃ ደርግ ለህወሃት ከበው ህወሃት የሚጠፋበት ጉድጋድ ይቆፍሩ ነበር ። በወቅቱ ህወሃት የሚቆረጠም ድርጅት አልነበረም ለሁሉም አሸንፎ ወጣ ። እዚህ ላይ መጥፎ ይሁን በጎ አላማ ይዞ በመናባት አሸንፎ መውጣት የህወሃት አመራርና ሰራዊት ባህሪ ነበር በጀግንነት አይታማም ነበር ። ሆኖም ግን ሻእብያ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ህወሃት የሚቀበርበት ጉድጋድ ሲምስ የህወሃት አመራር ጥቂት ካድሬዎች ሎሌኖታቸው ለመረጋገጥ እየሰገዱ እያሉ የሻእብያ ጌታ አዳሪነታቸው ለመረጋገጥ ሲባል በ1969 ዓ.ም ከነሃሴ መስከረም ወር በሻእብያ ጉባኤ በኤርትራ ነፃነት የሚረጋገጥ 30 ገፅ በላይ ፅሁፍ የድጋፍ ደብዳቤ ካነበበ በኋላ ታማኝነቱ ሎሌነቱ አረጋግጧል ። በወቅቱ የኢ.ህአፓ ፣ኢ.ድዩ ፣ሜኤሰን ኤርትራ ነፃ ሃገር ናት ከቅኝ ገዥዋ ኢ.ትዮጵያ ነፃ መውጣት አለባት ብለው ዕውቅና ባለመስጠታቸው ባለመደስኮራቸው ባለመደገፋቸው ኢ.ትዮጵያዊ ታማኝነታቸው በመረጋገጣቸው ካሳህል ፓርቱ ሱዳን ከ400ኪሎ ሜትር በላይ ምድረበዳ ተጉዘው ፓርቱ ሱዳን ገብተው አዳሩ ፡ የህወሃት መሪዎች አባይ ፀሃየ የሚመራው ቡድን ዘርአይ አስገዶምና ተወለ ወለማርያም ያሉበት ሰተሰምሃል ተነጠፈላቸው የዋሆች ጋዱች አገር የሚሸጡ ያሉ መሆናቸው አለማወቃቸው ወይም ሆን ብለው ገምጋሙ ለአንባብያን ታዱያ ኮነሬል ጎረሳ ምን እያሉ ነው
- የጅብሃን ማጥቃት በሚመለከት አሁንም ለማረጋገጥ በወቅቱ ሻእብያ ከ1970 ዓ.ም እስከ 1972 ዓ.ም ከገርሁ ሰርናይ እስከ ሳህል ተራራዎች ሲሸሸ የነበረው ሰራዊት በደርግ እየተጨፈጨፈ በሳህል ቓጠኝ እንደ ዝንጀሮ ተንጠልጥሎ በደርግና በጀብሃ ተከቦ ነበር በዛን ጊዜ የሻእብያ

ሰራዊት ሊዋጉ የሚችል በየቃጠኙ የተንጠልጠለ ከ10 ሺ በታች ነበር በመሆኑ ሻእብያ ለማዳን የሻእብያ መሪዎችና የህወሀት መሪዎች የትግራይ ህዝብና የህወሃት ታጋይ በማያውቀው በረቀቀ መንገድ

2.3.1 ከትግራይ ብዙ ወጣት ወደ ህወሃት ስለተሰለፈ ስንቅ ስለሌለ ማሰልጠኛ በረሃ ስለጠበበ ስህል ሂዶ እንደሰለጥን ከሰለጠነ በኋላ የመከላከል ውጊያ ተሞክሮ እንዲያገኝ ከሻእብያ ሰራዊት ተቀላቅሎ የውግያ ቀጠና እንዲሸፍን ተብሎ 1ኛ ዙር በሚያዝያ ወር 1972 ዓ.ም 3900 ሰልጣኝ ሰልጥኖ ወደ ሻእብያ ምሽግ የገባ እኔ ራሴ ያስገባሁት ኮኔሬል ያውቃሉ አብረን ተጉዘን እኔ ወታደራዊ አዛዥ ሁኜ በ1973 ዓ.ም ህዳር ወር 2800 ትግራይ አፅረጋ ስልጠና የጨረሹ በሳህል ንኡስ ፈግኮት በተባለ ምድረ በዳ ተጨማሪ አሰልጥነን ምሽግ ገባ አዛዞች ወታደራዊ መሪ አስገደ ገ/ስላሴ ፓለቲካዊ ሃላፊ ሰዓረ ማ/ከም ነበር አሰልጣኖች ጠርጣራው ግርማይ ጣጢቅ ሓጎስ አብርሃ ሓጎስ ዘገምቦ ወዱራማ ፣ያሉዋቸው 90 በላይ ረዳት አሰልጣኞች የነበሩት በ1973 ዓ.ም 2400 ሰልጣኞች ወታደራዊ አዛዥ አስገደ ፓለቲካዊ ሃላፊዎች ሰሎሞን ተስፋይ ሰዓረ በ1974 ዓ.ም ታህሳስ ወር በቀይ ኮኮብ ዘመቻ ዋዜማ 4000 ወንዶች 300 ሴቶች ድምር 4300 ስልጠናቸው አፅረጋ ትግራይ አገባድደው ለቀይ ኮኮብ ዘመቻ ለመከላከል በመሄድ መደበኛ ሰራዊት ለሞተውና ለቆሰለው መተክያ ተጠባባቂ ሰራዊት አለፎቆየ ይህ ሰራዊት መርቶ የተጓዘ ያለምብርሃን በዛብህ ( ዘገንባ) ወታደራዊ አዛዥ የኮነሬሉ በወቅቱ በስርቆት ወዳጁ የነበሩ ኋላ ህጋዊ ሚስታቸው የነበሩ ወ/ሮ ብርትካን ፍስሃ የሴቶች መሪ ሌሎች ከ120 አሰልጣኞች ይዘዋቸው እንድሄዱ እኔ ራሴ ሸኝኋቸው በወቅቱ የማሰልጠኛ ወታደራዊ አዛዥ ሆኜ ኮኔረል ያውቃሉ እሳቸው ይመሩት የነበሩ 2500 ሰልጣኝ የታመሙና የደከሙ ህፃናት ሲቀሩ እንዳሉ ተጉዞዋል በወቅቱ ኮኔረል እኔ ልሂድ ብለው ጠይቀው አይሆንም ብየ አስቀርኋ ቸው ። በአጠቃላይ ከዘመቻ ቀይ ኮኮብ በፊት ሳህል ገብቶ የሻእብያ መከላከያ ቀጠና ሊጠብቅ የገባ ሰራዊት 13400 ሰራዊት በወቅቱ የሻእብያ ሰራዊት 7500 ብቻ ነበረ በሬሾ ሁለት ለአንድ አካባቢ ነበር።

2.3.2 ጀብሃ በሚመለከት ሻእብያ ለጀብሃ እንዳይመታው ሰራዊት የለውም ስለሆነ የህወሃት ሰራዊት ከቀይ ባህር እስከ ሱዳን እንዲ ጠራርገው ከዛ በኋላ ሽእብያ ስትንፋስ እንዲያገኙ ተወሰኗል። በዛመሰረት

- ከቀይ ባህር እስከ ስራዩ ሓየሎም የሚመራው ከ6000 በላይ ሰራዊት የተሳተፈ ጠራረገው
- ቆዮት ብለው በሃምሌ ወር ከሰራዩ እስከሱዳን 7000 ሰራዊትና ብዙ ምንሻዎች አሰልፎ እስከ ሱዳን ጠራረገው በጀብሃ ጦርነትም እንዴት እንደተቀናጀና እንደተፈፀመ በሚገባ አውቃለሁ ደረጃዮም የሚፈቅድልኝ ነበር።

2.3.3 ህወሓት ለጀብሃ ለቀይ ኮኮብ ዘመቻ ለሰላህታ ዘመቻ መድምሰሱ ለህወሃት ጥቅም ወይስ ለሻእብያ ይላሉ ኮኔሬል

- እዚላይ መለሱ አንድና አንድ ለሻአብያ ጥቅምና ሂወት መዳን ነው የተደረገው ኮኔረሉ ራሳቸው እንዳረጋገጡት ህወሃትና ሸአብያ በወታደራዊ ስትራተጅና ፓለቲካዊ አቋሞች እስትራተጅካል ልዮነት እንደነበረባቸው አረጋግጠዋል ታድያ መሰረታዊ ልዮነት እያለ በአላማ የማትገናኘው ድርጅት እንዴት በአሰርሺዎች የሚቆጠር ሰራዊት ወደ እሳትይገባል ሻአብያ ጠላት ነው ሻአብያ ለኛ የሚያደርገው አስተዋፅኦ ትርጉም የለውም እየተባለ ሰራዊታችን ለምን ሳህል ገባ እየተባለ በህዝብ በታጋይ ጥያቄ ሲያቀርብ ብዙ ታጋዮች ህዝቦች ሳህል የሂደት ታጋዮች ወላጆች ሚስቶች ታስረዋል ተገልለዋል ተቀጥተዋል ጥያቄ ያነሱት ታጋዮች፦

1. ሓዱሽ ውነህ ከአድዋ በከባድ እስር ታስረዋል አሁን በሂወት አለ
2. ብርሃነ መለሰ (ሞርተር ከዓድዋ ከባድ እስር አሁን አለ
3. አለማዮህ ገዛሂይ ከሽሬ ታስራል አሁን አለ
4. መኮነን ዘለለው ከሽሬ አሁን አሜሪካ አለ
5. ግርማይ ጀርመን ከዓድዋ አሜሪካ አለ
6. ሙሉ አረጋዊ ከመቀሌ -ወደ አሜሪካ አምልጧል
7. አማረ አረጋዊ ከመቀሌ ታስራል
8. ተክለማርያም ተስፋይ (ዓወት) ታስሯል
9. ፋኑስ በላይ ከተንቤን
10. ሃይለስላሴ ኦልድ ማርክሲስት ከአድዋ ታስራዋል* ሌሎች ታጋዮች ህዝቦች ተሰቃይቷል ሌላ ቀርቶ በስደት ለነበሩ አባላት እንግልት ደርሶዋል
11. በ1973 ዓ.ም ሃምሌ ወር የህወሃት የሰራዊት ኮንፈረስ ከ300 በላይ ታጋይ ተሰብሳቢ ለብዙቀናት ዋነኛ አጀንዳ አድርጎ የተወያዩበት
    1) የኤርትራ ነፃነት ጉዳይ ለምን የባህር በር ወዘተ የሚሉ ጥያቄ አንገብጋቢ ነበር
    2) ሰራዊታችን በማናምንበት ስትራቴጂ ለምን ሰህል ገባን ሌሎች ጥያቄ ተነስተው

የህወሓት መሪዎች ግን የህዝቡን ጥያቄ በማፈን ስለ ሻአብያ ያነሳ ሁሉ መልሱ መውቀስ መገለል መታሰር መቀጣት ነበር ። ይህ ኮነሬል እርስዎ ያውቃሉ በማሰሩም በማጋለጡም ዋና መቺ ሓይል ሆኖ ነበሩበት እነ ብሰራት አማረም ዋና ተዋናኝ ነበሩ ኮነሬል ይትባረክ (ጎረሳ) በ1969 ዓ.ም እርስዎ በነበሩባት ሃይል 92 ቀውስ ፈጣሪዎች (ሓንፈሽቲ ) ( አንጃ ተብሎው እርስዎም ጭምር እየጠቆሙ ስለ ኤርትራ ጉዳይ የህወሀት አቋም በመቃወም ስለ ዲሞክራሲ ስለሰብአዊ መብት ለተማጎቱ እነ ኪዳነ ግርማይ ፣ታደሰ ዕንቍቂት ከመቀሌ እነ ኪዳነማርያም በላይ (ቀበሮ) ከአክሱም ወ.ዘተ እንዲታሰሩ ላላደረጉም አሁን ጳጳስ የሻአብያ ጠበቃ ሆነው መቕረባቸው ለምነው አሁን ያለነው 69 ዓ.ም አይደለም ሁሉም የተደረገው ያገረሸበት ሴራ እየሆነ ነው ።

2.3.4 የሚገርመው ነገር ግን ኮነሬል፣ አስገደ በሻአብያ በህወሓት የነበረ ግንኙነት ሲተነትን የነበረው ስልጠና ቦታ ለዚህ ሁሉ ለማወቅ ያስችለዋል ወይ ይላል በገፅ 2

- እኔ ሴራ አይደለሁም የህወሃት ሰራዊት በሙሉ የትግራይ ህዝብ ምንሻዎች የገጠር ካድሬዎች ነዋሪ ህዝብ የህወሃት መሪዎች በስልጣን ያሉና የሌሉ ምኒስትሮች የጦር አዛዦች ይመሰክራሉ ህወሃት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የደርግ ስርዓት እስኪወገድ ድረስ

1. በህወሃት አመራርና በብዙ መካከል አገናኝና ሁሉም ነገር ለማወቅ እድል ነበረኝ ማ/ኮሚቴ ባልሆንም ከፓሊት ቢሮ የማያንስ ምስጢር አውቃለሁ ለተሰጠኝ ስራ በታማኝነት እሰራለሁ ከፍተኛ አመራር የሚደብቁኝ ነገር አልነበረም ኮነሬል ያውቃሉ በ10 ሽዎች ስለጣኖች እየመራሁ ከህዝብ ጉዳይ አስተዳዳሪዎች ከስራዊት የነበረ ግንኙነትና የሴራ ቁርኝት የቀረበ እንደነበር ኤርትራ የገባ ሰራዊት በሚመለከት ከቀይ ኮኮብ ዘመቻ በፊት የገባ 13400 ታጋይ እኔ ራሴ ነው አሰልጣኝ ያስገባሁት አዛዥ ሁኜም እመራው ነበር ለቀይ ኮኮብ ዘመቻ የዘመቱ 3 ብርጌዶች 4500 ሰው ስንቅ ያዘጋጀነው አፅረጋ ነበር ኮነሬሉም ለከቸሮ የሚሆን እንጀራ ጋግረው አድርቀው እንዲያቀርቡ ያዘዝኮዎት እኔ ነው ። ወደ ተራ ነገር ወረድክ እንዳይሉኝ እንጂ ከእርሶ ጋር የማያሰማማኝ የነበረ እንቅልፍ ስለሚወዱ በሚበላም በሚጠጣም ነገር ስለማያስችሎት እንደዚሁ እኔ እንደማይተኛ የነበርኩ ያውቃሉ ሁሉ የህወሓት ታጋይ ይመሰክራል።

- ኮነሬል በህወሓት የሚሰሩ ከባድ ስራዎች የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ይህ ስራ ማን ይፈፅማል ሲባል መጀመርያ ወደ አእምራቸው የሚመጣላቸው አስገደ ነበር ለምሳሌ ለተወሰነ ለመጥቀስ

1. ወደ ኤርትራ ማን ይሂድ አስገደ ሂድኩ
2. የፀለምት ጦርነት በተደራቢ ስራ የሰራዊት ጭንቅና ስንቅ አስገደ ተባለ
3. ከባድ የድርጅት ምስጢር ስትራተጂክ ሪዘርቭ ማን ይስራው አስገደ
4. የ1980 ዓ.ም ማጥቃት ስንቅና ንብረት ትራንስፓርት አስገደ ጦር ግንባር በመዝለቅ
5. ዘመቻ ሰላም በትግል ከማይጨው ስሜን ሽዋ ወሎ ኃይንት ስንቂ ንብረት ትራንስፓርት አስገደ ጦር ግባር በመዝለቅ
6. የውጭና ያገር ውስጥ ትራንስፓርት ከፓርቱ ሱዳን ትግራይ 1982 ዓ/ም ታሪካዊ ስራ የተሰራው በአስገደ
7. ዘመቻ ዋለልኝ እስከ ዘመቻ ወጊገን ቀደምሊል ዘመቻ ቴድሮ ስንቅና ትጥቅ ትራንስፓርት ሃላፊ ጦር ግባር በመዘለቅ
8. 1977 ዓ.ም የድርቅ ጉዳይ መፍታት
9. 1981 ዓ.ም 60.000 ሰልጣኝ 25000 መርከኞች ስንቅ ህክምና ትራንስፓር በልዩ ተማድድ የሰራሁት - ይህ ሁሉ አያስፈልግም ነበር ሃቁን ለመግለፅ አስገደ ተዋጊ አዋጊ አስለጣኝ ሃኪም ሆኜ ሰርቼለሁ

ስለሆነም ኮነሬል ይትባረክ (ጎረሳ) ሁሉም ነገር እያወቁ አድርባይነታቸው ለማረጋገጥ ነው የሚናገሩት ያሉት ሌላ ሰው እንዳይደናገር ግን ሃቁን ይህ ነው ። ያልተነገረ እንጂ አስገደ የማያውቀው ነገር አልነበረም ኮነሬልም ሃቅ ለመናገር ዝግጅ ስላልሆኑ እንጂ

- እስከ አሁን ድረስ የገለፅኩት ኮነሬል የህወሃት አአማራር ሎሊ አይደለም አስገደ የትግራይ ህዝብና ታጋይ እስከ አማራሩ ሎሌ (አሽከር አድርጎታል ብለው ተቆረቆሩ በዚህ ፅሁፍም በኢትዮጵያ ራስ አሉላ አባነጋ ፓሊቶክ በርሀ ሃጎስ (ቦምባ ) በሚያስተባብረው ትቱላቸውን ነፍተዋል ። ነገርግን እስከአሁን የገለፅኩት ለህ.ወ.ሃ.ት የሻአብያ ሎሌ ያስበዋል ? አያስብለዋም የሚለው ነው ለዚህ ጉዳይ አንባብያን ገምግሙና <u>አስፋት</u>

3. ኮነሬል ይትባረክ ሻአብያ ለመዳን ኤርትራ የገባ ሰራዊት ቁሱልና ሙውት 27 ነበር ይላል አስገደ በዛን ጊዜ ስንት ሰራዊት ነበረን ነበረ ስንል? በተጨማሪ ከአቶ ሕቡር ገብረኪዳን በቦታው የነበረ ኤርትራ የተከፈለ መስዋእት 400 ሰው ብቻ ነው ብለውናል አስገደ ከየት አመጣው በኢትዮጵያ ራስ አሉላ አባነጋ ( በርሀ ሓጎስ)

- ኮነሬል ይትባረክና ሊንጎ ሻዓብያ አስገደ የትነበር የኤርትራ በርሃዎች እንዴት ያውቃል ይላሉ

3.1 እኔ የምለው ያለሁት ሻአብያ ለመዳን ለጃብሃ ጠራርጎ ሱዳን ያስገባ ከቀይ ኮኮብ ዘመቻ በፊት በ1972፥ 1973. 1974 ዓ.ም ለሻአብያ ቂጥ ጠባቂ የገባ ኣዲስ ምልመላ የትግራይ ወጣት ሻእብያን ለመዳን አንደኛ ዙርና 2ኛ ዙር ወደ ጀብሃ በዘመተ መደበኛ ሰራዊት በቀይ ኮኮብ ዘመቻ የተሰለፈ ሰራዊት ፣ በሰላህታ ወራር የተሰለፈ በሁለቱ ዘመቻዎች የተሰው ታጋዮች መተክያ በየጊዜው ሲሄድ የነበረ አዲስ የሰለጠነ የትግራይ ወጣት ተደማምሮ በተለያዩ ወቅት ኤርትራ እየገባ ፣እየወጣ የነበረው ሰራዊት ከ65 ሸህ ሰራዊት በላይ ነው በዛ የሞተው የቆሰለው የተማረከው በብዙ ሺ የሚቆጠር ነው ። አቶ ህቡር 400 ብቻ ሞተ የሚሉት እውነታቸው ያሁላ ወጣት ሲያልቅ እሳቸው ስላልወለዱት ምናቸው አይደለም እሳቸውም ተላላኪ ሆነው ሳህል ገብተው ነበር ። ወደ ጦርነት ግንባር ግን ተጠግተው አያውቁም ሳህል የነበረ አሁን በሂወት ያሉ እን ጀነራል ሳምራ የኑስ ጀነራል ሰዓረ መከነን አባሳደር አውዓሎም አርከበ ዕቁባይ ሌሎች ያውቃሉ አቶ ህቡር በትግራይ ከማዘዝ ማእከሎች ሆነው መላላክ ካልሆነ ወደ ህወሃት ከተቀላቀሉበት ጀምሮ እስከ ደርግ የሚወገድ የጥይት ጭሆት ሰምተው አያውቁም ይህ ሁሉ የህወሓት አመራር ይመሰክራሉ ። ወደ ኤርትራ ገብቶ ሲወጣ የነበረ የህወሃት ሰራዊት ብዛቱ የሞተው የቆሰሎው እየመሩ ወደ ጦርነቱ ያስገቡት የነበሩና የት እንዳለቀ የሚመሰክሩ አሁን በሂወት ያሉ መሪዎች

1. ጀነራል ሳሞራ የኑስ
2. ጀነራል አበበ ተሃይማኖት
3. ጀነራል ሰዓረ መኮነነን
4. ጀነራል ፀጋይ ፓትሪስ
5. አቶ አረከበ ዕቁባይ
6. አምባሳደር አውዓሎም ወልዱ
7. ኮነሬል ፀጋይ ማርክስ
8. ስምረት ወዲሚዶ አሜሪካ አሃዱ ያለ
9. ሻለቃ ገብረሂወት ወዲ ጨበር
10. ኮነሬል ሃዋዝ ወልዱ
11. ጀነራል ታደሰ ወልዱ
12. አቶ ይሳቅ ቀማጥ
13. ኮነሬል ጣቀም
14. አቶ ረመፅ
15. ጀነራል የውሃንስ ገ/መስቀል
16. ያለም ብርሃን ዘገንቦ
17. ኮነሬል ተፈራ ታደሰ
18. ኮነሬል ግርማይ ገብረስላሴ ጠውቅ
19. አቶ ፀጋይ ሰው ስቀል
20. አባዲ ትራፊክ
21. አፈወርቅ ተስፋንችአል
22. አቶ ታደሰ ደበሱ
23. አቶ ስብሃት ነጋ
24. ዶክተር አረጋዊ በርሃ
25. ዶክተር ግደይ ዘርአይፅዮን
26. አቶ አባይ ፀሃየ
27. አቶ ስዮም መስፍን
28. አቶ ስየ አብርሃ
29. ጀነራል ፃድቃን
30. ኮነሬል ጎሊያድ
31. እነ አማረ ዝንጉሪሒ ሌሎች ሃኪሞች

- የህወሃት ማ/ኮምቴ በሙሉና አሁን በሰራዊት ውጭና በሰራዊት ያሉ ባለስልጣናት የሚያረጋግጡት ነው ኣስገደ የት ነበር የሚለው ኮነሬል እንደሚያውቀው እሳቸው በነበሩበት በአንደኛ ዙር ወደ ምሽግ የገባ 3900 ሰራዊት በ1970 ዓ/ም ከእገላ ከደርግ የተማረከ ሻአብያ ይዞት ሸሸቶ የነበረ ውሰዱት ብለው ያን ትጥቅ ለማምጣት ይዘነው የሂድን 3200 ታጋይ ድምር 7100 ይዘነው የገባን እኔ አዛዥ ሁኜ ስንመለስ ወንዞች ሞልተው ሳህል እንዲከርሙ ሻአብያ ታጥቆ የሚመለስ ሰራዊት ወደ ትግራይ

እንዳይመለስ ለደርግ ሚስጥር በማሳለፍ የምንመለስበትን መንገድ ከከረን እስከ ዓፍዓበት ያለው መንገድ 60 ኪሎ ሜትር በደርግ እንዲዘጋ አደርጎት ። እኛ ሳህለ አንከርምም ብለን ጠላት የዘጋው መስመር በ30 ኮሎ ሜትር የተዘረጋ በመደምሰስ 140 ታጋዮች መቶውን 80 ቆስለው ተሻግረን በዛወቅት ኮነሬል ይትባረክ አንድ ሻንበል ጦር ይዘው ተደብቀው ነው የዋሉ። ያን አስቸጋሪ ችግር ተሻግረን 3 ቀን ተጉዘን በኋላ አድርሰን እንዳረፍን ከአየር ደብዳብ ጥንቃቄ አድርጉ ብለን ትእዛዝ ሰጥተን ስናበቃ ሁሉ ሰራዊት በሚገባ ተደብቆ እያለ ።

- ኮነሬል ይትባረክ የያዙት 150 ሰው ያላት ሻንበል በገላጣ ቦታ ምግብ ሰርታ እየበላች ድንገት ተዋጊዎች መጥተው ደበደቧት 76 ሞቱ፣ 48 ቆሰሉ ኮነሬል ሰራዊታቸው በገላጣ አስቀምጠው ሲጨፈጨፍ እሳቸው የተሰራላቸው ምግብ እየበሉ በዋሻ ተሸሽገው ተረፉ።በምግብ አያስችላቸውምና ኮነሬል በዚህ የመስመር ዓፍዓበት በኋላ የተሰዋ የቆሰለ ስንት ነው 343 ዶርሳል የህወሓት ሰራዊት በሳህል 4 ዓመት ከዘጠኝ ወር ሲቀመጥ ስንት ሞተ ስንትስ ቆሰለ ታሪክ ፃሃፊዎች ይመራመሩበት ።
- ሌላ ኮነሬል ይትባረክ አቶ ሊንጎ ከሰያትል በንኡስ ፈለከት በዓራግ ሁለት አመት ሙሉ ሰራዊት እያስለጠንኩ ወደ ምሽግ አላስገባሁም በምሽግ የነበረ 13400 ታጋይ በየግንባሩ አስተባባሪዎች መድቤ የሻአብያ ሂወት አላዳንኩም ።አቶ ሊንጎ እነ ሳህለ ብዙውም አታውቀውም በሃዘሞ እየተሽለክለከ የኤርትራ ህዝብ የምታሰቃይ የነበርከ ነህ ።የኔ ሻአብያ ለመዳን በሚደረግ የነበረ ስራ የነበረኝ ሚና የህወሓት መሪዎች የሻአብያ መሪዎች ያውቃሉ እነ ሊንጎ ምን ለማለት እንደፈለጋችሁ ግለፅ አይደለም
- እኔ እኮ የሻአብያ መሪዎች በሰራዊታችን ላይ የሚፈፅሙት የነበሩት ግፍ በመቃወም ለምን ሰራዊታችን ከአላማችን ውጭ መስዋእት ይከፍላል ከሻአብያ ምሽግ ንውጣ የሚል ጥያቄ በማቅረቤ ሻአብያም ለሚያደረጉት ሻጥር በመቃወሜ ስለከሰሱኝ የህወሃት መሪዎች እና ስብሃት ነጋና ግደይ ዘርአፅዮን የሻአብያ ሎሌነታቸው ለማማላት ከሳህል እንዲጠረዝ ተደረገ ይህ ኮነሬል ይትባረክ (ተክሌ ጎረሳ ) ያውቃሉ በዚህ ያገረሸበት ሴራ በተቀናጀ ለጋህድ መፅሄፎቶች የተሰናዱት ሃቀኛ ታሪኮች ለማድበስበስና ወደ ትውልድ እንዳያለፍ የሚንቀሳቀሱ ያሉት እነማናቸው እስቲ አንባብያን ትእዛዝ ብቻችሁን ሰንዝሩ እነማንስናቸው ።

<u>የድራማው ተዋንያን</u>

1. ደራሲ የውሸት ምንጭ ኮነሬል ይትባረክ አማረ ታሪካቸው በዚህ ፅሁፍ መግብያ ተገልፅዋል
2. ድምፃዊና አቀንቃኝ ሊንጎ የሻአብያ ታጋይ የነበረ ከሰያትል
3. አቃናባሪዎች የህወሓትና የሻአብያ መሪዎች

4. ሊቀመነኩሰችና አዝማሪዎች የድምፅ ሬድዮ አሜሪካ የትግርኛ ፕሮግራም ሃላፊዎች በትረስልጣን የህወሓት ካድሬ ተወለ ወልደገብርኤል የሻአብያ አባል በዋሽንግተን የሚኖሩ
5. ሰክስፎንና ትራንቢ ተጫዋች ኢትዮ ራስ አሉላ አባነጋ ከካናዳ የፓልቶክ ሚድያ አዘጋጅ ታሪኩ በመግብያ ፅሁፍ አለ
6. ቤዝ ጊታር ተጫዋች ድምፅ ወያነ ትግራይ ሬድዮ ጣብያ ከመቀሌ የሚመሩት የህወሀት ፓሊት ቢሮና የህወሃት ፅሕፈት ቤት ሃላፊ ቴድሮስ ሓጎስ ዳይሬክተር አበራ ተስፋይ ዓድዋ
7. ክራር ተጫዋች ብስራት አማረ ከአሜሪካ ኦሃዮና አጋሮቹ
8. ፒያኖ ተጫዋች ዓይጋ ፎረም አዲስ ወጣት የነ ህወሓት አባል ታማኝ ሚድያ
9. አስተዋዋቂና የመድረክ መሪ የደገሰው ደጉተር አለም ሰገድ መንገሻ (ነጠበ) ከ u s a
10. የሙዚቀኞች ደራስያን መጫወቻ መድረክ
10.1 ድምፅ ወያነ ስቱድዮ ከመቀሌ
10.2 ድህረ ገፅ ዓይጋፎሮም
10.3 ኢትዮራስ አሉላ አባነጋ ፓልቶክ (በርሀ ሓጎስ) ከከናዳ
12. አጃቢዎች ከበሮ ደላቂዎች
1. አቶ ሕቡር ገብረኪዳን ከደቡብ አፍሪካ
2. አቶ ወ/ገብርኤል ታደሰ ከመቀሌ

- የተከበራቹ አንባቢዎች ከላይ የተጠቀሱ የድራማና የሙዚቃ ተጫዋቶች እስከ አሁን የተነተንኩትን አይታችኛለ ቀጥሎ ወደ ሌላ አርእስት ከመሻገሬ በፊት የኮነሬል ይትባረክ ፅሁፍ የሊንጎ ሻአብያ ለድምፅ ወያነ ሬድዮ ጣብያ ከላይ ለተጠቀሱ የድራማ ተጫዋቶች ደካማ ጎናቸው ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ጎናቸው ጠቆም አድርጌ ልለፍ ።

<u>ጠንካራ ጎናቸው</u>

1. ለጋህድ መፅሃፍቶች ለመምታት ተነስተው ሳይታወቅባቸው ህወሃትና የሻአብያ መሪዎች ለአመታት ደብቀውት የቆዮት ሴራ እንደ አዲስ እንደያገረሽ አድርገዋል ። ለተማራማሪዎችም ምን እየተባለ ነው ብለው ጥያቄ አንስተው ሊያስቡ አስችላል ።
2. የኢትዮድያ ህዝብ የጋህድ መፃህፍቶች ይዘት ምንድነው ብሎ ሴራውን ሊያውቅ ጥረት እንዲያደርግ አስችላል
3. የትግራይ ህዝብ ልጆቼ ለምን ኤርትራ ወደቁ ብሎ ጥያቄ እንዲያስነሳ አድርጋል ።
4. ሻአብያ ለመዳን ኤርትራ ገብቶ ያለቀ ኢትዮድያዊ ለምን የሚል አዲስ ጥያቄ ሊያገረሽ አስችላል
5. ኮነሬል ይትባረክ በጣም የረከሰ አስተሳሰባቸው ሲገልፁ ።
   1) ህወሃት ለመጀመርያ ጊዜ ከሻአብያ ጋር ባይለማመጥ

2) 1967 ክረምት ለሙሴ ከእሱር ቤት ለማውጣት የአክሱም ኦፐሬሽን ለማካሄድ የሻአብያ እርዳታ ባይኖር አይካየድም ነበር አሉ ።
3) ኦፐሬሽን ያካየዱት ታጋዮች በሻአብያ ባይሰለጥኑ ኖሮ ድል አያገኝም ነበር ይላል በገፅ ሦስት ፅሁፋቸው ።

- ኮነሬል ይትባረክ እያሉን ያሉ ህወሓት የሻአብያ ታዛዥ ሎሌ መሆኑ በወቅቱ ትክክል ነበር እያሉ ነው የሚያስቡ ሰው መልስ ይስጣቸው ሞኝ ሁሉ ጊዜ ሞኝ ነውና
- የአክሱም የሽሬ ኦፐሬሽን ሊፈፀም የቻለ ሻአብያ ስላሰለጠኑን ነው የሚሉት
- ሃቁ ግን በሁለት ከተሞች ለማጥቃት የገባነው ለምን በዛው ኤርትራ ያልሄድን የደደቢት እያሰለጠን ነበርን ለምሳሌ አክሱም የገባነው
    1. አስገደ ገ/ስላሴ
    2. ግደይ ዘርአፅዮን
    3. አረጋዊ በርህ
    4. ነፃነት ሃይለ
    5. ንርአ
    6. ብርሀነ መስቀል
    7. ካሕሳይ በላይ
    8. ተስፋይ ወስላሴ
    9. የሓላሸት ገ/መድህን

    10፡ፀጋይ ቆቃሕ ደደቢት ብአስገደ ገ/ስላሴ የሰለጠነ ነበር ሌሎች 6 ሰዎች ከኤርትራ 2 ሰሞን ሰልጥነው ከመጡ በኋላ ለአንድወር እኛነን ያሰለጠንናቸው ።
- በዉግያ መሳርያ አክሱም የነበረ የራሳችን ብረት አንድ ግንፅል አንድ ከርባዮን አንድ ገጀራ አንድ ኩዚ አንድ ሽጉጥ ነበር ከሻአብያ ከተሰጡት ብረቶች 3 ብቻ ነበሩ የሁለቱ ከተሞች በታጋያችን ፅናትና ራሳችን በሰጠነው ወታደራዊ ስልጠና የተገኘ ድል ነው ኮነሬል ሃቁን ሸፍኖ በሰነበተበት የትግራይ ህዝብ ጀግንነት ቆራጥነት ሙያ ነጥቀው ለሻአብያ ለመስጠት የሚጥሩት ለምን እንደሆነ አይረዳኝም ትእዝብቱ ለአንባብያን በኔ እምነት ግን ለዛ የሻአብያ መሪዎች ያልሰሩት ስራን እያሉ የሚኮፈሱበት ድጋፍ እየሰጡ ነው ።
- ኮነሬል በገፅ 4 አዲስ መስመር ሲወሰን አስገደ በመጀመርያ ትግል ሲጀምር እርዳታ አያስፈልግም ከሻአብያ ግንኙነት አያስፈልግም ነው የምትለው ምን መሆን ነበረበት ትላለህ?
- እኔ ግንኙነት አያስፈልግም ስልጣን እርዳታ አያስፈልግም ነበር አላልኩም ሁሉም እርዳታ ያስፈልጋል እኔ የምለው ያለሁ ህወሓት ኢትዮጵያ ድርጅት ሆኖ ደግሞ የአንድ ብሄር ድርጅት ሆኖ ምንም ስልጣንና ሃላፍነት የሌለው ።ኤርትራ በወቅቱ ኢትዮጵያዊ እያለች የማይመለከተው ሻአብያ ሊያግዘውና ሊያሰለጥነው ሲል ምንም ታሪካዊ መነሻ የሌለው ኤርትራ ሃገር

ናት ከቀኝ ገዥዋ ኢትዮጵያ ነፃ ለመውጣት የምታደርገው ትግል ትክክል ነው ብለው ገፀ በረከት ይዘው ነው የሄዱት በተጨማሪ የህወሃት የትግል ፕሮግራም ምንም ታሪካዊ መነሻ የሌለው ትግራይ ነፃ ሃገር ናት የምናካይደው ትግል ነፃ ሪፐብሊክ ትግራይ ለመመስረት ከቀኝ ገዥዎች አማራ ነፃ ለመውጣት ነው ብሎ የሻእብያ ፕሮግራም ኮፒ በማድረግ 35 ፕሮግራም አሰራጭታል ታድያ ኮነሬል ይትባረክ ይህ ጉዳይ የህወሃት መሪዎች ሎሌ ብቻ ሳይሆን በርያ አያስብልም? ስለሆነ እኔ ያልኩት ግንኙነቱ አገርና ታሪክ የሸጠ መሆን አልነበረበትም ደግሞ ህወሓት ፕሮግራሙ ጭምር ሎሌ ነበር ። ምክንያቱ ፕሮግራም የሻእብያ ቅጅ ነው።

- ኮነሬል ህወሓት ነፃ ሪፐብሊክ ትግራይ ለመመስረት የሚል ፕሮግራም ለ 6 ወር ብቻ የቆየው ተሎ ብለው የታረመ ነው ይላሉ። እኔ እስከ 1977 ዓ/ም ሃምሌ ወር የህወሃት መሪዎች ሁለት ኮንፎረስ ሁለት ጉባኤዎች አልፈዋል ብዙ ሰሚናሮች ነበሩ በካድሬ ትምህርት ይነሳ ነበር መሪዎች አንድ ቀንም ሂስ አድርጎ አያውቅም። ኮነሬል እባክዎት በሺዎች የሚቆጠሩ ነበር ካድሬዎች አሉ ማን ይመሰክርለዎት አይሆንም ውሸት ነውና ። ኢህአፓ የሚያነሱ የነበሩና ወደ ጦርነት ያስገባ ነጥብ አንድ ይህ የኢትዮጵያ ታሪክ ማፍለስ ነበር።
- ኮነሬል ይትባረክ በራዛ ዘመቻ ጦርነት ዋዜማ ለራዛ መከላከል የነበረ ውል ይጠቅሳሉ ።።
- ኮነሬል በወቅቱ ገና አልታገለም ከአንድ አመት በኋላ ነው የታገሉ ከላይ እንደገለፅኩት አስገደ የት ነበር እያሉ የሰውን ጥረትና ትግለ ሲክዱ እሳቸው ግን ባልነበረበት ሲመሰክሩ ለማያውቃቸው ሰው ሃቅ ይመስለዋል ።
- እንግዲህ እኔ በራዛም በነበልባል ዘመቻዎች በዛላንበሳ በገር ሁሰርናይ ነበርኩ ሓኪምና ኣዋጊ ነበርኩ ዉሉ የተገኘ ትጥቅ መድፍ ካልሆነ መካከለኛ ከባድ ብረትና ቀላል ብረት ተተካሾች ጀብሃ ሻእብያ ህወሃት እኩል እንደሚከፈሉ ተስማሙ ጦርነቱ ተደርጎ በሺ የሚቆጠር ቀላልና መካከለኛ ብረቶች በሚልየን የሚቆጠር ብረት ተገኘ ታጋዩ በውሉ መሰረት አካፍሉን አሉ ሁለቱ ድርጅቶች በአመፅ ወሰዱት ሌላ ቀርቶ የህወሓት 3 ሻንበሎች ማለት 21 /11 ጢሒሳ የሚባሉ የህወሃት ሸንበሎች በየነበሩበት የማረኩት ሻእብያ አምጡ አሉን የህወሓት ታጋይ አንሰጥም አለ የህወሃት መሪዎች ሂወታችን የከፈልንበት አስረክባቸው አሉን 21ኛ ሻንበል አንሰጥም አልን ሌሎች ሃይሎች አስረከቡዋቸው። የህወሓት አመራር ተቆጡ ግን 21ኛ ሻንበል አልተንበረከከም እምቢ ብሎ ቀረ 11ኛ ሻንበል ጢሒሳ ያሁሉ መስዋእቲ ከፍለው ዉሃ ዘግነው ቀሩ ሎሌው የህወሓት አመራር ሻእብያ ያዘዙት እሺ ባይ እንደነበር ይህ አንድ ማስረጃ ነው ታድያ ኮነሬል እንደዚህ አይነቱ ሎሌነት እያዩ ለምን ለሻእብያ ይጠበቁለታል ።

- ኮነሬል ይትባረክ ሰላይ በነበሩበት ተንበርካኪነታቸዉ ሲገለፅ የህወሓት መሪዎች በዛን ወቅት ለሃይለኛው ሻዕብያ ፈርተው በትእግስት ማለፋቸው ትክክል ነበሩ ይላል በተጨማሪ በዛ ወቅት ለህወሓት ዘመናዊ ብረት አያስፈልግም ከአቅሙ በላይ ነበር መኪኖቹም ሊጠቀምባቸው አይችልም ነበር ብለውናል።
- አንባብያን በዛወቅት የህወሓት ታጋይ ወደ 350 ዶርሰዋል ያ አይችለውም የሚባለው ብረት M14 A60 ማትረዩስ ድሽካ 60 ሚሊ ሚትር ሞርተር 81 ሞርተር 50 ካሊበር አርፐጂ ሬድዮ መገናኛ ነበር ይህ ሁሉ አቅማችን ነበር ሰራዊታችን ታጥቆት የነበረ ብረት ጋንዴ ከዝ አላቢን ምንሽር የጣሊያን መትራዩሰች ቢዘንትና ለጀራ የሚባል ከ35 ኪሎ ግራም በላይ ክብደት ያለው ነበር በተጨማሪ በጣም ኋላቀር ግንፅል (ሽ ) ነበር።
- መኪኖች ቢሆንም ወደ ሱዳን አስጠግተን ለንግድ እናሰማራቸው ነበርን ከሽሬ የወሰድናቸው መኪኖች በምእራብ ትግራይ እስከ ሱዳን እናንቀሳቅስ ነበርን ታድያ ኮነሬል የሻአብያ የህወሃት አመራሮች ተደብቆ የማይደበቅ ሴራ ለመሸፈን ህዝብ ለምን ያደናግራሉ? በጋህድ ያለው ካርድ በትእግስት አንብበው ከአድርባይነት ነፃ ሆነው አንብበው እንዴት መልካም ነበር።
- ሌላ ኮነሬል ያልተረዱት ነገር አለ ሻአብያ ህወሓት ከተፈጠረበት ሦስት ወር በኋላ ጀምሮ በኢትዮጰያ የነበሩ ፀረ ደርግ ሃይሎች ለደርግ እያዳከሙለት ነገር ግን እርስ በእርሳቸው ግን መቃቃርን እየፈጠሩ እርስበእርስ እንዲጋጩና እንዲባሉ ዋና ጥረት ነበረ ወይ እንደ የህወሓት አመራር ፍፁም ሎሌ መሆን ነበረበት ህወሓት ደሞ ፍላጎታቸው ያማሉላቸው ነበር ።
- ኮነሬል በገፅ ስድስት ፅሁፍ አስገደ በ1968 ዓ/ም ህወሓት ከሻአብያ ጋር ሆኖ ለደርግ መደምሰሱ ስህተት ነበር ነው የሚለው ከባድ ብረት ብንካፈል የት እናገባዋለን የምናካሂደው ውግያ የደፈጣ ውግያ ስለነበር ምን ያደርግልናል? ቀዋሚ ማዘዣ ቦታ አልነበረንም ወስደን ብንቀብረውም አፈር ይበለዋል ምናልባት ሻአብያ ቢጠቀሙበት በመኪና የሚጎተት መድፍ ምን እናደርገዋለን ይላሉ ።
- ኮነሬል ጎረሳ አሁን ደሞ ደርግ ነበር ልትለኝ ነው የፈለግከው ደርግ መደምሰሱ አይቆረቁረኝም የሚገርማቹ ሙሴ ከእስር ቤት ለማውጣት የህወሓት የመጀመሪያ ጥይት እኔና ስዩም መስፍን ነበርን የተኮስናት በራዛና ነበልባል መደምሰስም በአዋጊነት ተዋናይ ሆኜ ተዋግቼ አዋግቼ ነበር።
- ብረት ያስፈልገን ነበር ይቅርና ዘመናዊ መትረየስ ለ40 አመት ተቀብሮ የቆዩ የጣለያን መትረየስ በናፍጣ አጥበን ትጥቃችን ነበር ለሌላ 17 አመት የትግል ጊዜ የደርግ ዘመቻ በመጣ ቁጥር ብዙ የመኪና ጭነት ስንቀብር እንደነበርና ተመልሰን እንጠቀምበት ነበር መድሃኒት ጥይት መድፎች የመኪና መቀያየርያ ዕቃዎች ወዘተ ተቀብረዋል ሌላ ቀርቶ የወፍጮ

መተሮች ይቀበሩ ነበር። ኮነሬል ተሳታፊ ነበር ታድያ ወንዝ የማይሻገር አሉባልታ ያወራሉ አሁንም ለህወሃት መሪዎች ከሎሌነት የምያድናቸው አይደለም እንግዲያውስ አንባብያን በኮነሬል ጉረሳ ትእዝብታቸው እንዲያሳርፍ ሚያደርጋቸው ነው።ኮነሬል ለህውሃት ኣመራርና ለትግራይ ህዝብ ታጋይ እንደፈለገው የሻእብያ ሎሌ ኣድርጎት ቀረ ብለዋል ይላል ኣስገደ።

- በመፃሃፍት የትግራይ ህዝብና ታጋይ ሎሌ ነው የሚል አንድም ቃል የለም ። የህወሃት አመራር ግን የህዝብ ተቃውሞ በታጋይ ጥያቄ በማፈን ሳያውቅ በመታለል የህወሃት አመራር ራሱ የሚቃወመው አላማና ስትራተጂ የሻአብያ መሪዎች ፍላጎት ለሚሟላት የትግራይ ወጣት እንዲያልቅ አድርጓል ።ለዚህ እንደ ምሳሌ

1. 1972 ፣1973 ፣ 1974 ዓ.ም ታጋይ ያለመሪ ሻአብያ እንደፈለገው ሊያድርጋቸው ወደ ምሽግ ሻአብያ ገብቶ የሻአብያ መሪዎች ተሞክሮ ልታገኙ ፊት ሂዳቹ ቃኙ ደፈጣ ውጡ ውሃ ተሸከሙ ቂጣ ጋግሩ እየተባሉ ለሻአብያ ከብርጌድ መሪዎች እስከ አንስተኛ ቡድን ታዛዦች ሆነው አገልጋይ እንዲሆኑ ተደርጋል።
2. በቀይ ኮኮብ ዘመቻ ወቅት የዘመቱ መደበኛ ከብርጌዶች በራሳቸው አመራር ተመርተው እንዳይዋጉ የህወሃት ብርጌድ መዋቅር ፈርሶ ተራ ታጋይ ከሻአብያ ታጋይ አንድ ለአንድ ተቀላቀለ ከቡድን መሪ እስከ ብርጌድ አዛዦች የሻአብያ ምክትል አዛዦች ሆነው እንዲዋጉ ተደርጎ የህወሃት ሰራዊት ቢቃወም እነ አቶ ስብሃት ነጋ ደኩተር አረጋዊ በርሂ ፣አቶ ስዩም መስፍን ሌሎችም ሳህል ድረስ ዘልቀው ለህወሃት ሰራዊት ሂስ ግለሂስ በማድረግ አሜን ብሎ በሻአብያ እንዲገዛ እንዲመራ ኣድርጋል የሻአብያ አዛገሮች እንደፈለጉት ኣደረጉት የበላይ ኣመራር ሆነው የሂዱት እነ አቶ አርከበ ዕቁባይ ጀነራል ሳሞራ የኑስ ጀነራል አበበ ተክለሃይማኖት የነ አቶ ስብሃት ነጋ መመርያ ተቀብለው ፀጥ አሉ ።
3. ከሰላህታ ወራር በኋላ ሰራዊት ህወሃት ከሳህል ወደ ትግራይ ሊሳብ ተፈልጎ ሻአብያ ከልክሎ እንደነበር የህወሃት አመራር ደብቆታል ከብዙ ንትርክ የህወሃት ሰራዊት ሊነሳ ከተወሰነ በኋላ የሻአብያ መሪዎች ሰራዊቱ ከመነሳቱ በፊት በሃልሃልና መካለሲ በርጀንገረር የነበረ የደርግ ሰራዊት ግዴታ ማጥቃት አለበት ተብሎ ጥናት በጎደለው የነበረ የደርግ ሰራዊት ግዴታ ማጥቃት አለበት ተብሎ ኣላስፈላጊ መስዋእቲ እንዲከፈል ተደርገዋል። በሺየሚቆጠሩ የህወሃት ታጋዮች ሞቶዋል ቆስለዋል ተማርከው መቀሌ የታሰሩ 400 ነበሩ በ1978 ኣጋኣዚ ኦፕሬሽን ተፈትዋል ይህም የህወሃት መሪዎች ታዛዥነትና ሎሌነት እንደነበር ያመለክታል ለተከፈለው መስዋእት እንደ ማስረጃ አቶ መድህን ኮነሬል ስምረት አምባሳደር አውዓሎም ጀነራል አበበ ተ/ሃይማኖት ሌሎች ጦር አዛገሮች በመከላከያ ሚኒስቴር የሚገኝ ያውቃሉ።

- ኮነሬል ይትባረክ ምን እያሉ ነው ይህስ ለሎሌነት አያስብለም ነው የሚሉን ። ይህም ለገምጋሚዎችና ተመራማሪዎች እንተወው።
- ኮነሬል ይላል በገፅ አስር አዲስ መስመር ሁለት ነፃ ሃገራዊ ሪፐፕሊክ ትግራይ የሚል ፕሮግራም ለአጭር ጊዜ ይዞ ቆይቶ ወዲያውኑ በ1968 ዓ.ም ታርሟል ይላሉ ።
- አረ ኮነሬል ትክክል አይደለም መቼ ነው የታረመው በየተኛው ጉባኤ ወይ ኮንፈረንስ ወይም ሰብሰባ ወይ በፅሁፍ፣ እኔ እስከ 1977 ዓ.ም ነሃሴ ወር የማለሊት ጉባኤ ሲነገር ሰምቼ አላውቅም አንድ የህወሃት ካድሬም አይመሰክርም።
- በ1970 ከኢህአፓ ጦርነት መነሻ የነበረ ከሃገራችን ውጡ እኛ ነፃ ሃገር ነን ውጡሉን አንወጣም ኣሉ የጦርነት የእልቂት መነሻ ለምን ኮነሬል ያልተፃፈ ያነባሉ ያልነበሩበት እርሶ ወደ ሰራዊት ህወሓት የተቀላቀሉ በ1969 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ነው። ልታድር ብለህ አይዋሽም ።
- ኮነሬል በገፅ 12/1969 በህወሃት ውስጥ የነበረ ቀውስ በፈሪዎች ጭንቀታሞች የሚፈጥሩ ውጅብር ነበር ይሉና ።
- ደጋግሞሽ ይሆናል እንጂ የ69ዓ.ም የቀውስ መነሻው የዲሞክራሲ የሉአላውነት ጉዳይ ነበር የነበረ ጥያቄ ነው ።

1. ህወሓት የሻአብያ መሳርያ ነው ለምን?
2. የኤርትራ ነፃነት ስንቀበል ምን ስልጣን አለን የኢትዮጵያውያን ጉዳይ አይደለም ብሄራዊ ፓርቲ ሆነን ስለ ሃገር ሙሉ ለመወሰን እንችላለን ወይ
3. የግንባር ገድል ሓርነት ትግራይ ( T.E.L.F)ለምን ተጨፈለቀች ይህ ደግሞ ፀረ ዴሞክራሲያዊ እርምጃ ነው ።
4. ከኢህአፓ ጋር ያለን ግጭት በሰላም እንፍታው
5. በህገ ደንባችን አንቀፅ የሌለ ለምን ወኪል አመራር ተሾመ፤ በጉባኤ ይመረጡ
6. የህወሓት አማራር በዘመድ አዝማድና በጓዳኝነት በአውራጃ የተመሰረተ ስለሆነ እንደ አዲስ ጉባኤ ይደረግ ወዘተ...

- የሚሉ ጥያቄዎች ነበሩ እነዚህ ጥያቄዎች ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎቸ አይደሉም ወይ? በኮነሬል ተክሉ ጎረሳ ግን ቀውስ ናቸው ትእዝብቱን ለአንባብያን እንተዎው ።
- ኮነሬል በገፅ 13 አዲስ መስመር አምሰት የሽራሮ ህዘብ በሻአብያ ላይ ግርግር ሲፈጠር የህወሓት አመራር የህዘብ ጅራት ሆኖ መሄድ ነበረበት ነው የሚለው አሰገደ።
- ኮነሬል በእርሶዎ አይንና አጋሮችዎ የህዝብ ሃሳብ መቀበል እንደ የህዝብ ጅራትና ሰርኣት አለበኝነት ይቆጥሩታል። ዴሞክራሲ አስተሳሰበና ተግባር የሚያምኑ ሰዎች ግን የህዝብ ሃሳብ መቀበል ማሳተፍ ህዝብ አስተያየት እንዲሰጥ ያምናሉ ። ሁሉም ኣይነት መብቶቸ ይፈቅዳሉ እርሱ እንደሚናገሩበት አሜሪካ የሚደረገው ያደርጋሉ። ኮነሬል እኔ የሚያሳዝነኝ

በአሜሪካ ሆነው እንደዚህ አይነት ፀረ ዴሞክራሲ መፃፍዎ ለአሜሪካ ህዝብም መንግስት ስማቸው እያጠፉ ነው።

- ኮነሬል እምነት ግን ህብረተሰብ ስለማያውቅ እኛ እናውቅሃለን ባልንህ መንገድ ተመራ ካለበለዝያ አትኖራትም ብዙሃኑ ይመኑ አይመኑ ገደል ይግቡ ነው ይህ ባህል በህወሓት አመራርና ጥቂት ካድሬዎች እንደመግለጫ ሆኖ ሲተገበር የነበረ ነው ይህ ደግሞ ፀረ ዲሞክራሲ ፀረ እድገት ነው ።
- ኮነሬል አስገደ በ1969 ዓ.ም በህወሓት ውስጥ የነበረ የተጨናነቀ የጠበበ ሁኔታ ከማንም በላይ ያውቀዋል በጣም ተቆርቃሪ ነበር ብቁ እንደነበር አምናለሁ ነገር ግን ከነዛ ጥቂት ድክመቶች ጥቂት አንስቶ ማስጨለም የህወሓት ሌሊ ሻአብያ ነበር ማለቱ ትክክል አይደለም ይላሉ ጎረሳ በገፅ 14 አዲስ መስመር ሰባት።
- እኔ ስለ 1969 ቀውስ ከፍብሎ በቂ መልስ ሰጥቻለው ኮነሬሉ ዋና ችግራቸው ህወሃት የትግራይ ህዝብ ህወሓትና የህወሓት አመራር አለመለየታቸው ነው ችግራቸው የትግራይ ህዝብና የህወሓት ታጋይ ፀረ ፋሽሽት ደርግ በትክክል መስዋእት ከፍለዋል ጀግና ነው ያደረገው ትግልም ቅን ነበር የህወሃት አመራር ካድሬዎች ለትግራይ ህዝብ እንደ አንድ ሰው አንቀሳቅሰው ቢፈልጉ ለፓለቲካዊ ድርጅቶች መሳርያ መዘው ለመምታት ቢፈልጉ ለደርግ ማጥቃት ቢፈልጉ ለሻአብያ ሰራዊት በመስጠትም ብዙ መስዋእትነት ሊከፈል በማድረጋቸው ጠንካሮች ነበሩ። ግን ደግሞ የህወሃት አመራር የሻአብያ ሎሌ ለመሆን ሻአብያ ራሱ እንደሞልድ (ቅርፅ) የሰራው ነበር ነው የምለው ያለሁት ። እንግዲህ ኮነሬል ካላመኑ ለታሪክና ፓለቲካ ሳይንስ ተመራማሪዎች እንተውላቸው ።
- ኮነሬል በገፅ 16 አዲስ መስመር አራት አስገደ መፅሃፍ ሙሁራን ገመገሙት ይለናል እነዛ ሙሁራኖች በጋህድ ሓቅን የቀበሩ ናቸው ወይ ሌላ ሰዎች ይላሉ
    1. መጀመርያ ህወሓት አመራር ለሙሁራን ይቅርና ለታሪክ ሙሁራኖች ታሪክ ፃፍ ብሎ ሊሰጥ ጭራሽም አያምናቸውም ብዙ የታሪክ ሙሁራን እንደነ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀኝ በ1986 ዓ.ም ታሪክ ሊፅፍ ጠይቆው ሂድ የት የነበርክ ነህ ህወሓት ታሪኩ ራሱ ይፅፈዋል ብለውታል ለሌሎችም ኮነሬልም ለሙሁራኑ ያለዎት ክብር ተመሳሳይ መሆኑ አውቃለሁ።እኔ በመፅሃፎቼ ሙሁራን ፈትሸውታል አስተያየትም ሰጥተውበታል የሚል አንድም ቃል የለውም በመግቢያዎች የተፃፈው ፅፌው ያለሁ መፃህፍት የማውቀዉ ያየሁት በተግባር የነበረኩበት ራሴ የታሪክ ሰነድ ነኝ ይላል።
- ቀጥሎ የዚህ ፅሁፍ አለማ የታሪክና የፓለቲካ ሳይንስ ተመራመሩበት መጥፈውና በጎው ትውልድ አውቆት በጎው ስንቅ እንዲሆነው መጥፎው በሙዜም ገብቶ እንዳይደገም እየረገመው እንዲኖር ይላል እንግዲህ ኮነሬሉ

ይትባረክ ዝም ብለው ከጀርመን የነጠቃት ዶላር እየበሉ ላለፆት በሽታ በየአመቱ ደምዎን እየቀየሩ እድሜዎን እንደማስረዘም አካል ጉዳተኛነት (ዲስ ኤብልነኝ) እያሉ በአሜሪካ ጥሮታ ነጥቀው ኢትዮጵያ ለመግባትና ብለው መንግስት ታርቀው ለመኖር ነው መሰለኝ ይህ ሁሉ የሚዘላበዱ ያሉ።

- እንደኔ ምክር አድርባይነት ትተው ወደ ኋላ መለስ ብለው ያሰለጠኑት ወጣት ስለህዝብ ብሎ ሻአብያ ለመዳን በመላእ ኢትዮጵያ ፀረ ደርግና ሌሎች የተሰዋ ያለቀ ህዝብና የወደመ ንብረት እያስታወሱ ታሪኩ ቢፅፍና ለሚፅፍ ቢያበረታቱ መልካም ነበር ።እንደ ጋህድ መፅሃፍቶች ታጋይ ህዝብ አንብቦታል የሰጠኝ አስተያየት ካለ በርታ ብቻ ነው ያለው እነዛ በመፅሃፍ ተጠቃሽ የሆኑትም ባለሰልጣኖች ያሉት ነገር ቢኖር አስገደ ጥሩ ሰነድ ፅፉል ደካማ ጎኑ ጊዜው ያልጠበቀ ምስጢር አወጣ ነው ያሉት አሁን ግን ሚስጥር የሚሉ እኛ ካለፍን ሰነዱ የት ይገኝ አልመለሱትም ኮነሬል ወደዱም ጠሉም ጋህድ 1.2.3. መፃህፎች የህወሃት የትግራይ ህዝብ ታሪክ የመአዝን ድንጋይ መሆናቸው አረጋግጣል ።
- ኮነሬል በገፅ 17 አዲስ መስመር አራት ሸአብያ ለትግሉ ከድቶ ከደርግ ጋር ቢታረቅ ለህወሃት ብዙ ችግር ይደርስበታል ነበር ሻአብያ ከደርግ ጋር ቢታረቅ ኖሮ ደርግ ያለውና የሎሌው ሃይል ሰብስቦ ለህወሃት ያጠፋው ነበር ይላሉ ። መልስ ይቀጥላል
- ይህ አባባል ዋና መደናገርያ የህዝብ አስተሳሰብ ለመቀልበስ የመጣ ነው ሻአብያ ለህወሃት የከዳው አንድ ሁለት ጊዜ አይባልም ብዙ ጊዜ ከድቶታል ለዚህ ምሳሌ ።
    1. በ1969 ዓ.ም ኢድዩ ለህወሃት ሲያጠቃት ሸአብያ ከኢህአፓ በመቀናጀት ህወሃት እንዲጠፋ በሻለቃ የተደራጁ ሰራዊቱ ይዞ ኢህአፓ ለህወሃት እያሰፈራራ ተንቀሳቅሷል።
    2. በ1970 ዓ.ም የሰሜን ወራር አብረን እንከላከል ብሎ በገርሁሰርናይ በራማ ኣሕስኣ ተሰልፎ ህውሓት ያለው ሃይል አሰለፈ ብዙ ታጋዮቹ ካለቁ በኋላ ሻአብያ ሳይናገር ከደርግ የተነጠቀ ከ40 ሽህ ብረት ከባድ መከላከያ ቀላል መሳርያዎች ሬድዮ መገናኛ ይዞት ሸሸ በተጨማሪ በጦርነት የቆሰሉት የህወሃት ታጋዮች በመቶ የሚቆጠሩ ይዙዋቸው ሸሽቶ አብዛኛዎች ሞቶዋል ጥቂት ድነው ከአመታት በኋላ ተመልሰዋል ደርግ በትግራይ ለህወሃት ሊያጠፋ የሚችል አንድ ግብረሃይልና ሁለት ንኡስ ግብረ ሃይል(44ሽ) ሰራዊት ትቶ ሄዶ ህወሃት ግን ክረምት ሙሉ ለዛ 45 ሰራዊት አድክሞት በጥቂት ካንፓች ቁጭ ሊያደርገው ቻለ። ቀጥሎ ጀቦ ደመና ገለጥ ነበልባል የሚባሉ ሰራዊቶች ከኤርትራ ሳበ እነሱም 1971 ዓ.ም በህወሃት ሰራዊት ተሸነፉ 1972 ብዙ ሰራዊት ወደ ትግራይ ተሳበ 6ኛ ዘመቻ በመላው ትግራይ ዘምቶ በየዘመተበት ተመታ። -

ህወሃት በኤርትራ በጎንደር በወሎ በውስጥ በደርግ ሰራዊት ተከቦ እየተዋጋ ሰፊ ነፃ መሬት ሲፈጥር ሻአብያ ከ1970 ዓ.ም እስከ 1972 መስከረም በሽሽት ነበር ያሳለፈው። ታድያ ኮነሬል ጎረሳ የህወሃት የኣመራር ስህተት በዚህ ጊዜ ያላጠፋ መቼ ነው የሚጠፋ የህወሓት አመራር ስህተት ለመሸፈን ያልሆነ ውጅንብር ለምን ይፈጥራሉ?

3. በ1977 ዓ.ም ደርግና ሻዓብያ ለመታረቅ በሚደራደሩበት የትግራይ ህዝብ በድርቅና በርሃብ እያለቀ እያለ ህውሃት ህዝቡን ለመዳን ስለሄደ እርዳታ ሰጭዎች ያቀረቡለት እህል በልቶ ሂወቱ ሊያድን ጉዞ ጀምሮ ወደ 50 ሺ ህዝብ ከሰላ እንደገባ ደርግ ያን አጋጣሚ ተጠቅሞ ከወሎ ከመቀሌ ወደራያ ከመቀሌ ወደ ተንቤን ከአድዋና ከዓድግራት ለእገላ ፣አሕሰአ ከአክሱም ወደ ዛናና ዓዴት ሁሉም ተሰብስበው በሽሬ በእንዳባጉና በማይፀብሪ ፣በዓዲዳዕሮ በበረንቱ በቆሓይን ከሕሞራ ሁሉም ወደ ደደቢት ሽራሮ ወልቃይት ሊዘምቱ ጉዞውን እንደጀመሩ ከመላው ትግራይ ሂወቱን ለማዳን በአድያቦና አስገደ ተሰብስቦ ተራ በተራ ኤርትራን አቃርጦ ወደ ከሰላ ሊገባ 10 ኪሎ ሚትር ቀርቶት ሊገባ ከመቶ ሺ ህዝብ የሚበላ የፌኖ ክምር አሻግሮ እያዩ የሻእብያ ፋሽሽት ድርጅት ሰራዊት አሳልፎ ወደ ኋላ ተመለሱ አላቸው ያቺ ሉጃ ሻአብያ ለማዳን ሳህል የሞተ ልጅ 40 ዲግሪ በላይ ሙቀትና ርሃብ ውሃ ጥም ያጠቃት እናት ህፃናት አዛውንት ሻአብያ ተመለሱ ሲላቸው ሲጓዙ ኣድሮ ሜዳ የነጋበት ጅብ ሆኑ። ተመለሱ እንደማይመለስ የለም የኤርትራ ህዝብ የተሰኔ ሃይኮታ ተከንብያ ተው ወንጀል ትፈፅማላችሁ ሲላቸው ብዙ አዛውንትና ሽማግሌዎች ታሰሩ ።

- ህዝቡ በደርግ ሚጎች እየተደበደበ እንደቅጠል እየረገፈ የኮሌራ በሽታ ወባ ታሞ በየመንገዱ እየረገፈ እየሞቱ በዚህ ጉዞና በተከዜ ወልቃይት ሻአብያ በፈፀመው ወንጀል ከ70 እስከ 100 ህዝብ ሞቷል ያ በተከዜና በወልቃይት የተከበበ ህዝብ በከባድ ችግር ወደቀ።
- ደርግ ከበረንቱ ከቖሓይን ከዓዲኻላ ወደ ትግራይ ሲዘምት የሻአብያ ሰራዊት ዝምብሎ አሳለፈው በየ ተራራዎች ሁኖ በሬድዮ መገናኛ በመለጠፍ የህወሃት ሞት ያዳምጥ ነበር ።
- ጦርነቱ በሁሉም አካባቢ ተጀምሯል የህወሓት ሰራዊት በምእራብ የነበረ ግማሽ ሃይሉ ሊዘምተው የመጣ እየተከላከለ ግማሽ ሰራዊቱ በባዕኸር በዳንሻ በዓብደራፍዕ በዓንገረብ የነበረ የደርግ ሰራዊት በመደምሰስ መንገዱ በመክፈት በተከዘ የነበረ ስደተኛ በብዙ ችግር ሱዳን ገባ ከኮሌራና ከውሃ ጥም ወባ ምት የተረፈ በብዙ መቶሺ ሰፋዋና ወደል ከወሊ ሌሎች ቦታዎች ገባ ዳነ ።

- ደርግ በየዘመተበት አከባቢዎች የህዝብና የህወሃት ንብረቶች ቤቶች አቃጥሏል እንስሳ ዘርፏል ። በሁሉ ቦታ ግን ተሸንፏል ብዙ ሰራዊቱ በውግያም በበሽታም አልቋል የነበረ ጭንቅ በ3 ወር ውስጥ ተፋታ ። በመፅሃፎቹ ደርግና ድርቅ ሻእብያ ግንባር ፈጥረው ለትግራይ ህዝብ ፈረዱበት በሚል ርእስ በስፋት ተፅፋል ተመልከቱት።
- ታድያ ኮነሬል ሰራዊታችን ሻእብያ ለማዳን ሳህል ብናስገባው ህወሃት ይጠፋ ነበር ይሉናል ከዚህ የባሰ ችግር ምን ኣለ ህዝባችን የፈጀ የሻእብያ ሴራ ። ሻእብያ ቢጠፋ በኛ ላይ የሚመጣ ችግር አልነበረም ሻእብያ እኮ ከሰላሕታ ዘመቻ በኋላ እስከ 1982ዓ.ም በኤርትራ ውግያ ኣላካሄደም ህወሓት ትግራይን የነበረ የደርግ ሰራዊት ጠራርጎ ካስወጣ በኋላ እንቅስቃሴው ወደ ሰሜን ሸዋና ጎንደር ጎጃም ወሎ እያሰፋ በሄደ ቁጥር በኤርትራ የነበሩ 604 607፤ 605፤ 608 ኮሮች 3ኛ፤11ኛ፣ 15ኛእግረኛ ክፍለጦሮች ከኤርትራ እየተሳቡ በህውሓት ሰራዊት ተመቷል በኤርትራ ጥቂት ሰራዊት ቀረ። ታድያ ኮነሬል ሻእብያ ኣስሮ የያዘው የደርግ ሃይል የትኛው ነው? እስቲ ወታደራዊ ጠቢባን ተርጉሙት ግን ኮነሬል ይትባረክ ኣጋሮቻቸው ሻእብያ ባይኖር ኖሮ እንጠፋ ነበር እያሉ ጡሩምባቸው እየነፉ ይኑሩ።

4. በ1983 ጥርና የካቲት ወር ሻእብያ የፈፀመው ክዳት ህወሓት ዘመቻ ቴድሮስና ቦሊሰማ ወለቂ ጢማ በምናጠቃበት በትግራይ ምንም መደበኛ ሰራዊት ባልነበረበት ደርግ ሁለት ክፍለጦር ከአስመራ በመንቀሳቀስ ዓድዋ አክሱም ሽሬ ተቆጣጥሮ ወደ ጎንደር በመገስገስ ጥቃቱን ለማክሸፍ ሲንቀሳቀስ ራማ ከደረሰ የትግራይ ምልሻ ገበሬና መጥረብያና ገጀራ ይዞ ሲተላለቅ ሻእብያ በቆሓይን ፃሮና ዓድኻላ አካባቢ 3 ክፍለ ጦር እያለው ዝም ብሎ ወደ አድዋ አሳለፈው። ይሁንና የትግራይ ህዝብ ዓድዋ ሳይገባ ኣገተው በሺ የሚቆጠር ታጋይ ምንሻ መቶ ቆሰሏል ።ታድያ ኮነሬል ሻእብያ መቼ ነው የህወሓት መኖር ፈልጎ የሚያውቅ? ታድያ ከዚህ የባሰ ተንኮል አለ? የህወሃት ድል የሚፈልግ ቢኖር ዘመቻ ቴድሮስ ለማክሸፍ ለተንቀሳቀሰ የደርግ ሰራዊት ማጥቃት አልነበረበትም?
5. በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባ ስንገባ 76 የከባድ ብረትና የህክምና ባለሞያዎች ተሳትፎዋል እነዚህ ሰዎች ሆን ብለው የያዙት መድፎች ታንኮች እንዲበላሹ አድርገው ምንም አስተዋፅኦ የሌላቸው የህወሓት መሪዎች ለርካሽ ፓለቲካ ሸዓብያ በባህርዳር በጎጃም በአዲስ አበባ ገቡ ተብሎ በሬድዮ ተገለፀላቸው ። በተጨማሪ አዲስ አበባ እንደገባ 300 የሚሆኑ የሻእብያ ካድሬዎች ሰላዮች ከአስመራ አዲስ አበባ በመግባት ንብረት መዝረፍና የሻእብያ ጠላቶች የሚሉዋቸው ኢትዮጵያዊያን እያፈኑ ወደ ኣሰብና ኣሰመራ መውሰድ ጀመሩ። ከታፈኑት ግን እኔ ራሴ በነበረኩበት ያዳንነው በርሀ ቀመም አንዷ ነው ሊመስክር ይችላል። ሌላ ወርቅና ባንክ ለመዝረፍ ሞክረዋል። በግለሰዎች ቤት እየገቡ መዝረፍ ንብረት ትጥቅ

ማውደም ፈንጅ መቅበር ስራችን ብለው ተያያዙት መኪኖች ከአዲስ አበባ እየሰረቁ ንብረት እየጫኑ ለአሰብና አስመራ ላኩ። በዛ ወቅት የህወሓት አመራር ምንም የወሰደው እርምጃ አልነበረም ኮነሬል ይህስ ምን ይሉታል? እዚህ ላይ ሎሌ ስራ አልተሰራም? መቼስ ኮነሬል አይዋጥሎትም ምክንያቱ አላማዎ በጌታዎ አድርባይነት ስለሚፈለጉ ።

6. የሻእብያ መንግስት ኤርትራ ከተቆጣጠረ በኋላ በተሰኔ፤ ባረንቱ፤ አቁርዳት፤ ከረን፤ አስመራ፤ ማስዋ፤ ዓሰብ፤ ደቀምሃረ፤ሰገነይቲ፤ ዓዲቀይሕ፤መንደፈራ፤ዓዲኻላ ከሌሎች ገጠር ኤርትራ የነበሩ የመንግስት ሰራተኛ ነዋሪች ነጋዴዎች ፣ወዝአደሮች ወታደሮች የወታደር ሚስቶች ቤተሰቦቻቸው ለእድሜልካቸው የተቀመጡባት አገራቸው ጥለው እንደወጡ ንብረታቸው ወርቃቸው ልብሳቸው ጫማቸው ሳይዙ የያዙት ገንዘብ ተዘርፈው አብዛኛው በእግሩ ወደ አድግራት መቀሌ ሽረ አክሱም ዓድዋ ሕሞራ ሚላ ኮምቦልቻ አዲስ አበባ በየሜዳው ተወርወሩ ደካሞች አዛውንት ነፍሰጥሮች ጭነት መኪና በየጠረፉ ተጣሉ ።እርጎዞች በመንገዱ ወለዱ ሞቱ በየኣረፉበት በተቅማጥና ከሌራ በብርድና ፀሃይ፤ ንፋስ ሞቱ ሃኪምና መድሃኒት አልነበረም።

- እኔ አጋጣሚ ከዘመቻው ተመልሼ የትራንስፓርት የስንቅና ትጥቅ ሃላፊ ነበርኩ ለስደተኛ ስንቅና መጣልያ የምናቀርብ እኔና ሌሎች እንደነ በያንፍትዊ፤ ያዞል፤ በላይ ኢማን ሌሎችም ነበርን ያሁኔታ ዘግናኝ ስለነበር ሪፓርት እናደርግ ነበር ። ህዝብም ያማርር ነበር ። የህወሓት አመራር የሰጠው መልስ ቢኖር አገራቸው ውጡላቸው እናንተ ኢትዮጵያውያን በትግሉ ወቅት ከደርግ ጋር ወግናችሁ አንደኛ ዜጋ ሆናቹ የቆያቹ ስለሆናችሁ ኣሁን ያእድል አታገኙትም ነው የተባሉት። ኤርትራ ሻእብያ ቢቆጣጠራትም ገና በህጋዊ መንገድ ያልተገነጠለች እንደዚሁ ውሳኔ መስጠት አስቀድሞ መፍረድ አይሆን ታድያ? ኮነሬል ለዚህ መልስ አለዎት? ከላይ ለተጠቀሱት ስድስት ነጥቦች የህወሃት ማ/ኮ ምን መልስ ሰጠው?
    1. በ1967 ዓ.ም ሻእብያ ለፈፀመው ተንኮል የህወሓት መሪዎች አሁንም ጌቶች እያሉ እጅ እየነሱ ሃገራዊ ጥያቄያችሁን እናምናለን ሌሎች የኢትዮጵያ ድርጅቶች የምንላቸውም ሲለማመጡዋቸው ነበር።
    2. በ1970 ዓ.ም የፈፀመው ክህደት የህወሃት መሪዎች አሁንም እየለመኑ ግንኙነታቸው አደሱ
    3. በ1977 ሻአብያ ከደርግ ጋር አብሮ በትግራይ ህዝብ ላይ የፈፀመው ስቆቃና ግፍ በጃማይካና ሰብሃት ነጋ ስዮም መስፍን አማካይነት ሱዳን ላይ እየተገናኙ በልመና በ1980 ግንኙነታቸው አሻሻሉ ።
    4. ሻአብያ 1980 ዓ.ም በራማ ያደረገው ተንኮል ህወሃት አቃልሎ አይቶ ዝም አለ

5. 1983 በዘመቻ ቴድሮስ ዋለልኝ የፈፀመው ወታደራዊ ተንኮል ምንም አልተጋለጠም
6. በ1983 ዓ.ም በአዲስ ኣበባ የፈፀመው ተንኮልና ኤርትራ በነበረ ህዝብ የደረሰ ግፍ ህወሃት ምንም ጥያቄ ሳያነሳ ዝም አለ በአንፃሩ ለትግራይ ህዝብ ስድብና ውርዴት ይሰነዝር ነበር።
7. አዲስ አበባ ለስርቅና ለተንኮል የገቡት በፈፀሙት ወንጀል እንደመጠየቅ ፋንታ በግብዣና በሽልማት ነው የሸኛቸው ።

- ታድያ ኮነሬል እነዚህ ተደማምረው የህወሓት መሪዎች ሎሌ መባል ያንሳቸዋል? እንግዲህ ለአንባብያን እንተውላቸው ።ሌላ የአቶ ሊንጎ ሌሎች ኤርትራውያኖች አስተያየት
- አቶ አስገደ ሽአብያ በቀይ ኮኮብ ዘመቻ ተሸንፎ ሱዳን ጠረፍ ተጠግቶ ነበር ይሉናል ብለዋል ፣በተጨማሪ አስገደ የት ሆኖ ነው ያዩው ይላሉ ። ሌላ የወያነ ሰራዊት ለስልጠና እና ለምድ ለማግኘት ነው ሳህል የገባ እንጂ ለሻአብያ ምንም ፋይዳ አልነበረውም ይላሉ ። መልሱ ግን
- 9. ሻአብያ በግንባር ብር ፣በዓራግ፣ በሓሊባች ሕሽክብ አግራዕ ንኡስ ፈለከት የነበሩት የተለያዩ የድርጅት ዋና ዋና ክፍሎችና ማዘዣ ማእከሎች ሸሽተው ዓራርብ እንደገቡ የሻእብያ ታጋይና ሁሉ ህወሓትም ያውቃሉ ።
- በምሽግ የነበረው ሰራዊትም ለሽሽት ተዘጋጅቶ ንብረቱ ሚያቃጥልበት ቤንዚን አዘጋጅቶ ነበር። የሻአብያ ስንቅ ትጥቅ ንብረቶች ለማሻሻት ወደ መኪና ጫኝና አውራጅ አዲስ መሸሻ መንገዶች በመጥረግ ተሰማርቶ የነበረ ወደ ጦርነት ለገቡት ብርጌዶች ሰምተውና ለቆሰለው ማከምያ ተብለው ስልጠና በትግራይ ይጨርሰው ተጠባባቂ ሰራዊት የነበረ የህወሓት ያልታጠቁ ተጋዮች ነበሩ።
- አቶ ሊንጎ ግንዮት ነበሩ አቶ ሊንጎ እኮ ከኣኩለግዛይ ወጥተው አያውቁም እዛው ሆነው ወጣቶች አዛውንት ሳይለዩ በግድ እያፈሱ ለሳህለ እየሸኙ የነበሩ ለህዝብ እያስገደደ ደሮ ፍየል እያማረጡ ሲበሉና የወንዶች ሚስቶች የሚያማግጡ እያስገደዱ የነበሩ ናቸው። አስገደ ሳህል አያውቅም ብለው አፋቸው መልቶው እንዴት ሊናገሩ ይችላሉ ።
- ሌላ አቶ ሊንጎ የወያኔ ሰራዊት ሊማር ይመጣ የነበረ እንጂ በጦርነቱ ወቅት የነበረው ድጋፍ ትርጉም ያልነበረው ነው ብለዋል። ይህ አባባል በዘመቻ ቀይ ኮኮብ ጊዜና ከዛ በኋላ ፕሪዝዳንት ኢሳእያስ ለውጭ ጋዜጠኞች ቀይኮኮብ ዘመቻ ማሸነፍ የቻላቹህ በህወሃት ሰራዊት ድጋፍ ነው ብለው ሲጠይቁ የሰጠው መልስ የወያነ ሰራዊት ለኛ ለማገዝ አቋምም ሞራልም የለውም ጥቂት ሰልጣኞች ሊማሩ የመጡ ነበሩ ሌላ ግን የምናውቀው ነገር የለም ሻአብያ የደርግ ወራር ለመመለስ በቂ አቅምና ሞራል አለው አሉ። ኢሳአያስ አፈውርቅ አቶ ሊንጎም በጌታቸው ሳምባ ቢተነፍሱ ችግር የላቸውም።

- ሌላ አቶ ሊንጎ አቶ አስገደ የፃፍት መፅሃፍ የኤርትራ ህዘብና ለትግራይ ህዝብ የምያቃቅር በታች መፅሃፍ ብለውታል
- ሰዎሰቱ ጋህዶች ለትግራይ ለኤርትራ ህዝብ የሚያጋጭ ነጥብ የላቸውም ለዚህ ማስረጃ መፅሃፎቼ ሁሉ ህዝብ አንብቦታል ሰለዚ ህዝብ ይመሰክር። አቶ ሊንጎ በአንባብያን ትእዝብት ወድቀዋል ። አቶ ሊንጎ ሻእብያ በሰርያ በኢራቅ ስለሰለጡኑ ለወያነ ለማሰልጠን በቂ ኣቅም ነበረው ይላሉ። እኔ የሻእብያ ኣሰልጣኞች ከሃፀይ ሃይለስላሴ እስከ ደርግ ሰርኣቶች በሃረር ጦር ሞኮነኖች ማሰልጠኛ በሆሎታ በኤርትራ ሞኮነኖች ማሰልጠኛ በኤስራኤላውያን የሰለጠኑ ነበሩ። ልክ ኤርትራ እንደነበሩ በህውሃትም ብዙ የትግራይ ተወላጆች ኣሰልጣኞች ነበሩ ኣንድ ነገር ግን ነበረ ሻእብያዎች ሲመኩበት የነበሩ ከኣረብ ሃገሮች እርዳታ ለማግኘት ሲሉ የኢራቅ በዓዝ ፓርት እና በኢራን፤ፓኪስታን ኣፍጋኒስታን ሱዳን ኣክራሪዎች ሳህል እየገቡ ሲጎበኙ ነበር። ኣክራሪዎች ለጉብኝት ሳህል ሲገቡ የሻእብያ ሰራዊት ሁሉ እስላም ነው ሊባል የኣረብ ቀሚስና የራስ ኮፍያ ሻሽ እንዲያደርግ ይገደድ ነበር። የህውሓት ታጋዮችም እንዲያደርጉ ወይ እንዲሸሸጉ ይደረግ ነበር አቶ ሊንጎ የሚኮፈስበት የኣረብ ወታደራዊ ሳይንስ ሰልጥለናል የሚሉት ውሸት ነው።

- ሌላ አቶ ሊንጎ ለህወሃት ሻእብያ ጠፍጥፎ እንድጭቃ እንደሰራትና ተሸክሞ አዲስ አበባ እንዳስገባት ደስኩረዋል ለዚህ መልሰ በጉዞው የህወሓትና የሻእብያ መደጋገፍ እንዴት እንደነበረ ተገለፅዋል ማን ለማን እንዳየነው አንባብያን ገምግሙት።
- ሌላ ቀን አንድ ኤርትራዊ ድምፅ ሬድዮ አሜሪካ ምንም እንካ እንደነ ሊንጎና አቶ ኢሳእያስ ባይክድ አንድ የተሻለ ምስክርነት መስክረዋል ። ይላል አቶ አስገደ 65 ሽ ሰራዊት ኤርትራ ገብቶ ነበረ ያሉት ስህተት ነው 4 ብርጌዶች እያንዳንዳቸው 1500 ጠ/4500 ገብተዋል ብሎዋል። ሌሎች የሻእብያ መሪዎች ግን ያ በ አስር ሺዎች መስዋእትና ጉዳት የተከፈለው ፈፅመው አያምኑን በዚያች ቀውጢ ጊዜ የህወሓት ታጋይ እንደ አምላክ ያዩት ነበር የሻአብያ መሪዎችና ካድሬዎች ትእቢታቸው እንዳይተነፍስ የህወሃት ታጋይ ወሳኝ አስተዋፅኦ ብክድት እንደዚሁ የህወሓት መሪዎች ብደበቁት የኤርትራ ህዝብ ግን ሻአብያ ከሳህል ጉድጋድና ቋጥኝ አውጥቶ ትንፋስ የዘራበት የህወሃት ታጋይ መሆኑ እጅጉን ያውቃሉ።
- ሌላ የህወሃት መሪዎች የሻአብያ ሌሎ መሆናቸው ማረጋገጫ
    1. የህወሃት መሪዎችና ካድሬዎች ህወሃት ከተመሰረተበት ቀን ጀምረው ኤርትራ ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ከሻአብያ መሪዎችና ካድሬዎች በላይ እየታገሉ እንደመጡ እንዳለ ሆኖ ሻአብያ ኤርትራ እንደተቆጣጠረ በመስከረም 1984 ዓ.ም ሻአብያ በኣል

በሚያከብርበት ከህወሃት አማራር አንዱ የሻአብያ ባንዴራ ሰቅሏል ይህ ተግባር አንድ ነገር በስተጀርባ እንደነበር ያመለክታል።

2. በኤርትራ ይኑሩ ለነበሩት ኢትዮጵያውያን ሻአብያ ግፍ ሲፈፅምባቸው ምንም አይነት ተቃውሞ አያሳይም ነበር።
3. ኤርትራ ልትገነጠል ሪፍሪንደም ሊካዮድ አካባቢ ስለመገንጠሉ ጉዳይ ከኢትዮጵያውያን ሙሁራኖች የታሪክ የህግ ባለሙያዎች በመመካከርና በማሳተፍ በጥናት የተመሰረት ሊካዮድ እንደመጣር ፈንታ ሁሉም ነገር የሻአብያ የህወሃት በነበራቸው የበረሃ አስተሳሰብ አሳፍሪ በሆነ ነገር ሪፍረንደም ተካይዷል።
4. ስለ ኤርትራ ሪፍረንደም የኢትዮጵያ ህዝብ በሙያ የተካኑ ሙሁራኖች የውጭ ዜጋ ባለሙያዎች ዲፐሎማቶች ያገር ሽማግሌዎችና ታሪክን የሚያውቁ የእድሜ ባለፀጋዎች ተው ጉዳዩ ሰከን ብላችቸሁ እዮት ጊዜ ሰጡት ብለው ምክር ሲሰጡዋቸው በተለይ ደግሞ እንደነ ደጃት ዘውዴ ገብረስላሴ በፅሁፍ በአካለ ሊምክራቸው ሞክሮው የሰጧቸው መልስ ቢኖር የህወሃት አማራር ለህዝብ ለታጋይ በካንፎረንስ በስሚናር በስብሰባዎች ይላሉ መስፍኖቶች ተዋላዋይ ሙሁራኖች ኢንፐራሊስቶች የኤርትራ ሪፍረንደም ይቆይ ታገሱ እያሉ ነው። ተመለሰው 30 አመት ወደ ውግያ ሊያስገቡን እኛ የማይቀየር አቋማችን ስለሆነ ኣንቀበላቸውም የኤርትራ ነፃነት እንዳይረጋገጥ እንቅፍት የሚፈጥር እንፈርዳቸዋለን ተባለ ።
5. ኤርትራ ስትገነጠል ኤርትራ የምትባል ከየት ወዴት ነው? ለሺዎች አመት የባህር በር የነበራት አገራችን እንዴት ትሁን? የኢኮኖሚ ግንኙነት በምን መንገድ ኤርትራ ከተገነጠለ የዜግነት ጉዳይ እንዴት ሊሆን ነው? የሪፍረንደም አፈፃፀም በምን ሰነስርኣት ይፈፀማል ወዘተ ጥያቄ ሳይነሳ ተድበስብሶ ሊታለፍ ተደርጋል ።
6. ከሻአብያ ጋር ይደረግ የነበረ ዲፐሎማሲያዊ ግንኙነት እስከ ኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ዋዜማ በህወሃት የአንደ ፓርት መሪዎችና በሻአብያ መሪዎች ነው ሲደረግ የነበረው ለምን? የሚለው ለአንባብያን
7. በኢትዮጵያ የነበረ ኢትዮጵያ የሪፍረንደሙ ጉዳይ ጥርጣሬ ስለነበራቸው ትገንጠል ብለው ለመምረጥ አብዛኞቹ ፍቃደኞች አልነበሩም ። የህወሓት አመራርና ካድሬዎቹ ግን ለኤርትራውያን በሰብሰባ በኮንፈርንስ በየቤታቸው በመስበክ ለመገንጠል ድምፃቸው እንዲሰጡ ግፊት ይደረግላቸው ነበር ።
8. ለሻአብያ ማቋቋምያ በዛን ወቅት ባዶ የገንዘብ ካዝና የኖራት ኣገር ብዙ ሚሊየን ብርና ዶላር ተሰጥቷል።

- ታድያ ኮነሬል ይትባረክ (ጎረሳ የህወሃት መሪዎች ለምን የሻአብያ ሎሌ ተባለ ብለው አካኪ ዘራፊ እያሉ የሚደነፍቡን ይህ ሁሉ የተተነተነ የኋላ

ታሪክ ጉዞ ስለማያውቁ ነው? አይመስለኝም ፍላጎታቸው ያቺ የህዝብ ዶላር በልተው ስለጨረሷት ምናልባት ከኢህአዴግ ታሰታርቀኝ ትሆናለች በሚል ተስፋ ነው ። እንደኔ ከሆነ ኮነሬል ለህሊናቸው ብለው ሃቅ መስክረው ቢያልፉ መልካም ታሪክ ይሰንድ ነበር ።

- ሌላ ኮነሬል ገፅ 19 አዲስ መስመር ሁለት ፅሁፋቸው ወንድማችን አስገደ እየታገለ እያለ የሚያምንባቸው የነበሩ ነገሮች አሁን ገልብጦ እያዛባ የሚፅፍ ያለው መልሱ ግልፅ ነው አስገደ አሁን ከህወሓት ስለሌለ እኔ ከመትኩ ስርዶ አይብቀል በሽታ ነው ያ በሽታ ግን በአስገደ ብቻ ያለ ሳይሆን በሌሎች ነበር መስራች ነን ባዮችም ያለ ነው ይላሉ ኮነሬል ጎረሳ።
- ይቅርታ ኮነሬል እኔን እርስዎ ያውቁኛል በትግል ወቅትም ቅር ያለኝ ነገር መሪ ነው ባለስልጣን ነው ስላለ እንደ እርሰዎ በማንም አመራር ተገፍቼ ማሞቅያ ሂተር ተደርጎብኝ ሰው የምጎዳ ወይ ራሴ ደፍቼ እምኖር ሰው አልነበረኩም ለሁሉ ነገር በግልፅና ጮህ ብየ የምናገር የፈለጉኩትን ስላደርግ እማልተኛ ለራሴ ታታሪ ሰራተኛ ሁኜ ለበላይና ለበታቼ ሰርቼ የማሰራ መሆኔ እርሶ ኮነሬልና መሬዎቼ የነበሩ የህወሃት ታጋይ ይመሰክርልኛል።
- ሌላ በ1985 ዓ.ም በህወሃት በአጠቃለላይ በኢህአዴግ ኮራብሽን ብልሹ አሰራር ፣ሃብት መካበት ፀረዴምክራሲ አሰራር ስለነበረ ስለ ኤርትራ ጉዳይ ጠንካራ ጥያቄ በማንሳት በተለይ ደግሞ በህወሃት አመራርና ካድሬዎች የነበረ ስልጣን በዘመድ ኣዝማድና በጋብቻ መተሳሰር ሲቢል ሙሁራንን የማግለል ሰራቶኞች እንደዜጋ ኣለማየት የኢፈርት ድርጅቶች ኣቃቃም ፍትሃዊነት በሚመለከት ከህውሃት የተጠቀሱ ታጋዮችና የሰማእታት ቤተሰቦች ልጆች ኣያያዝ በሚመለከት ጥያቄ ኣንስተው በ10ሺ የሚቆጠሩ ሰራዊት ከታሰሩ ከተባረሩ እኔም ኣንዱ እንደነበርኩኝ ኮነሬል ይትባረክ ያውቃሉ። እርሶም ጥያቄ በማንሳታቸው የታሰሩና የተባረሩ ዋና መቼ ሃይል እና ኣሳሪ ፈራጅ እንደነበሩ የመከላከያ ሚንስተር ጓደኞችዎ ያውቃሉ ኣርእስት እኔም ኣውቃለው። በጎንደር በባህር ዳር በሁመራ ዋና ኣፋኝ እና ኣሰሪ ነበሩ።

እኔ ከ 1986ዓ.ም ህውሓትን ትቼ ከወጣሁም ህውሓት ኢሃደግ ለማፅዳት በተለያየ የህዝብ መድሮኮች ሃሳቤ በመግለፅ በመንግስትና በግል ጋዜጦች ኣካል ጉዳቶኞች በሚመለከት ስለ ግፍ ኣያያዛቸው ሌሎች ኣፈናዎች በሪፖርተር ጋዜጣ ስለፍትህና መልካም ኣስተዳደር እጦት ስለ ነፃነትና የህግ የበላይነት ኣለመከበር በማህበራዊ ጉዳይ ስለህክምና ውሃ ኤሌትሪክ ኣገልግሎት እጦት በክልላችን እና በኣገራችን ሙሱና በሚመለከት በህዝባዊ ጋዜጣ ኣድማስ ኣዲስ ነገር ኢቶፕ ኣስተያየቴን በመግለፅ ታግያለሁ። ኋላም በግል ፓርላማ በመወዳደር በኢትዮጲያ በተለይ በትግራይ በሙሱና በልማት በዲሞክራሲ እና ፍትህ ያህገር ሉኡላዊነት ኢህአዴግ የሚፈፅመው ስህተት በማጋለጥ ታግያለሁ።

ዋና ኣብይ ጉዳይ ደግሞ የህውሃትን የ30ዓመት ጉዞ ታሪክ ጋህድ1.2.3 ሶስት መፅሃፍ በመፃፍ ለንባብ ኣብቅቼ ትውልድ ብዙ እንዲገነዘብ ኣድርጌአለሁ።

በኣሁን ጊዜም በፖለቲካና ስነ ሃሳባዊ በፖሊሲ ከኢህአዴግ የበለጠ ኣማራጭ ድርጅት ዓረና ትግራይ በሃገር ደረጃ ደሞ መድረክ ተደራጅቼ በሰላማዊ ትግል እታገላለው። እኔ እንደ እርሶ ኣሜሪካ ሆኜ ሳይሆን የመዶሰክሮው መቀሌ ሆኜ እታገላለው። ታድያ ኮነሬል እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል የሚል ኣርእስት ለኔ ይገልፀኛል? ፍርዱ ለኣንባብያን።

ኮነሬል በኔ እምነት እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል የሚል ኣርእስት ለእርሶ ነው የሚገልፀው። ም/ቱም እርሶ ያ መጥፎ በሽታ ታመው ጀርመን ሄደው እንድመመለስ በራሶ ኣመልካችነት ሚሊተሪ ኣታቼ መሆነዎ ኣልቃወምም ግን ደግሞ በኢ/ያ ህዝብ ምክንያት ከስደተኛ ህዝባችን የተሰበሰበ ዩሮና ዶላር ኣፍሰው ይዘው ኣሜሪካ ኮብልለው የህዝብ ገንዘብ መብላቶ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል የሚል ኣርእስት ይገልጦታል። ሁለተኛ ጋህድ መፅሃፍቶችን የህዝብ ትግራይና ትግሉ የሚገልፅ ሃቀኛ ታሪክ እያለ ለህውሃት መሪዎች ሎሌ መሆኖ ለማረጋገጥ ሲሉ የህዝብ ታሪክ ማበላሸትዎ ይህም እንደ ኣህያዋ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ ኣይብቀል የሚል ኣርእስት ይገልፆታል። ስለሆነ እባኮትን ኮኔሬል ተክለ ጎረሳ ለክቡርነቶ ሲሉ ሃቁን ይመስክሩ።

በመጨረሻ ምስጋና ለጋህድ ተቃዋሚዎች

ኮነሬል ይትባረክ ሆኑ ሌሎች ኣጋሮቻቸው እና በኋላ ሆነው ሊፅፉ የገፋፉቸው ኣካላት እጅግ እጅግ ነው የማመሰግናቸው ምክንያቱም

1. የሻእብያና የህውሓት የነበረ ግንኙነት ያገረሸበት ሴራ ሆኖ እዲጋለጥ ማድረጋቸው
2. ይህ ፅሁፍ በመፃፋቸው በሬድዮ በፓልቶክ የሚሰማቸውን መናገራቸው ያለፉትን 36ኣመታት የትግል ጉዞችን ቦጎውና መጥፎው ነጥቦችን ኣስታውሼ እንድፅፍ በማድረጋቸው
3. በህውሓትና በሻእብያ በነበረ ግንኙነት እንደኣዲስ እንዲገረሽ በማድረጋቸው
4. የኮነሬል ይትባረክ(ጎረሳ)፣ብስራትኣማረ፣ድምፅ ወያነትግራይ፣በትረ ስልጣን፣ ተወለ ወ/ገብሬኤል፣በርሀ ሓጎስ፣የኣይጋ ዌቭሳይት ኣዘጋጆች የህውሓት ቢሮ፣ ሕቡር ገ/ኪዳን፣ ኣለምሰገድ መንገሻ ወዘተ... ፀረ የህዝብ ትግራይ ታሪክ መሆናቸው በመጋለጣቸው
5. በነዚህ ሰዎች ባነሱት ኣጀንዳ ለመመለስ በቡዙ ሰዉ ህሊና የነበረ ጥያቄ ለመመለስ ስላስቻለኝ
6. በኤርትራ ሻእብያን ለማዳን ወደ እሳት የተማገዱ ስማእታት ተረስተው የነበሩ እኔና ኣንባቢዎቼን ልናስታውሳቸው በማስቻሉ።

*ክብር ለሁሉም ኣይነት ጭቆና ለማስወገድ ብለው ለተሰው ሰማእታት*
*በኣስገደ ገ/ስላሴ ወ/ሚካኤል*

**ከመቀሌ**
*ስ.ቁ +251(0)914757242*